# የሥነ - ጥበባት ትምህርት

## የመምህሩ መምሪያ 3ኛ ክፍል


**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች**

ደሜ ቶሊና

ሉባባ ጀማል

ታደሰ ድንቁ

**አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ደንደአ ቦጋለ

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሰን

**ተርጓሚ**

ሙሉቀን አብራሐም

**ኤዲተር**

ደቀቦ ጉዬ

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገላጭ ስዕል**

ቡዛየሁ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝቶ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# መውጫ


አጠቃለይ መግቢያ ........ v

_Toc115720686_ምዕራፍ 1 የሥነ-ጥበባት ግንዛቤዎች ........ 1

**1. የስነ-ጥበባት አይነቶችን መለየትና መግለፅ ........ 1**

1.1 የሙዚቃ ኖታዎች ........ 1

1.2 መሠረታዊ ቀለማት ........ 11

**1.3 የፎቶ አነሳስ ዘዴ እና የዲራማ ጫወታ ........ 18**

ምዕራፍ 2 : የፈጠራ ችሎታ ........ 25

2. የሥነ ጥበባት ልምምድ ........ 25

**2.1 የሙዚቃ ድምፆች፣ኖታዎች እና የምት መዚቃ መሣሪያዎች ........ 27**

**2.2 ቀላል የሆኑ ቅርፆችን ቀለም መቀባት ........ 36**

**2.3. የመሠረታዊ ቀለማት ድብልቅ እና ቀጥተኛ ህትመት ........ 42**

**2.4. የዲራማ ፣ቪድዮ እና ፎቶ መልዕክቶች ........ 51**

ምዕራፍ 3 : የባሕል እና ታሪክ ተጨባጭ ሁኔታ ........ 58

**3. የባሕል ዕሴት መግለጫ ........ 58**

**3.1 ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች ........ 59**

**3.2 የባሕላዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃ ታሪክ ........ 63**

**3.3. በትያትር የባሕል እሴቶች ከንዉን ........ 65**

ምዕራፍ 4 : የሥነ ጥበባት መሥዕብ........ 72

4 የሥነ ጥበባት ሥራዎች አድናቆት ........ 72

**4.1 የስነ ጥበብ አድናቆት** ........ 72

**4.2 የባሕላዊ ሙዚቃ አድናቆት** ........ 75

**4.3 ጫወታን በትያትር** ........ 77

ምዕራፍ 5 ፡ የሥነ-ጥበባት ትስስር ........ 82

5.1 ሥነ-ጥበባት መካከል ያለዉ ግኑኝነት ........ 82

**5.2 የሥነ-ጥበባትሌሎች ትምህርት መማር ዉስጥ ያለዉ አስፈላጊነት** ........ 84

## አጠቃለይ መግቢያ

በመማር እና ማስተማር ሂደት ውስጥ፤የእያንዳንዱ ተማሪ ተሳትፎ እንዳይወሰን፤መምህር ሁሉንም ቡድን በመቆጣጠር ፣መርዳት፣መምራት እና ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ስለዚህ መምህር/ርት በትምህርት ዉስጥ ሁሉም ተማሪዎች ሃሳብ በመስጠት፣መወያየት እና በመከራከር ዕዉቀት፣ግንዛቤ እና ያላቸዉን ልምድ በመለዋወጥ የሚፈለገዉ የትምህርት ዉጤት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ አለብህ/ሽ፡፡ መምህር/ርት የሥነ ጥበብ ትምህርት ሲታስተምር/ሪ መግቢያ፣አቀራረብ፣ማጠቃለያ እና ዓላማ ከማቀድህ/ሽ በፊት መፈፀም ያለባቸዉን ድርጊቶችን በደንብ ማዘጋጀት እና መፈፀም አለብህ/ሽ፡፡

### ሀ.በመግቢያ የሚፈፀሙ ድርጊቶች

ተማሪዎች ያለፈዉን የትምህርት ይዘት፤ በደምብ መማራቸዉን ለማረጋገጥ መምህር/ርት የተለያዩ ከትምህርቱ ጋር የተያያዛቱን ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ከዕለቱ ትምህርት ጋር ማያያዝ አለብህ/ሽ፡፡ በተለይ ለተጠየቁት ጥያቄዎች በተለያየ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች እድል በመስጠት፤ መልስ ላላገኙት ጥያቄዎች ደግሞ ጎበዝ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ ማድረግ እና ሁሉም ተማሪዎች ለትምህርት እንዲዘጋጁ፣ክፍል ዉስጥ እንዲሳተፉ፣ እንዲመወዳደሩ እን በትምህርቱ ጎበዝ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ከዕለቱ ትምህርት ጋር ተያይዘዉ፤ ተማሪዎች ቀድሞ ያላቸዉ ዕዉቀት (prerequiste knowledge) ማወቅ እና አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፤ተማሪዎች ሃሳብ እንዲሰጡበት በማድረግ እንዲሁም የዕለቱ ትምህርት ጠቀሜታ/ፋይዳ፣አስፈላጊነት እና ዓላማ ጋር በማስተዋወቅ ተማሪዎች እና እንዲዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

### ለ.በአቀራረብ የሚፈፀሙ ድርጊቶች

በመማር እና ማስተማር ሂደት ትምህርቱ ሲቀርብ

- በይዘት እና ዓላማ ላይ በመመሥረት፤ በአነስተኛ ቁጥር ቡድን በማደራጀት እና በርዕሱ ላይ እንዲወያዩ መምራት፡፡
- አንኳር የሆኔ የመወያያ ነጥብን ከትምህርቱ አጠቃላይ ዓላማ ጋር እንዲሄድ ለቡድኑ በተዘጋጀ ጥያቄዎች መሰረት በሳሌዳ ላይ መጻፍ፡፡

- *መምህር/ርት እያንዳንዱን ቡድን መማራቸዉን መከታተል፣መምራት፣ማገዝ እና መቆጣጠር አለብህ/ሽ፡፡*

**በቡድን እና ክፍል ዉስጥ ያላቸዉን የእያንዳንዱ ተማሪዎች ተሳትፎ መከታተል እና ማበረታታት፡፡**

- *በአነስተኛ ቡድን የተወያዩበትን ወይም የሰሩትን ነገር፤ ሁሉም የቡድኑ አባላት ተራ በተራ በተለያየ የትምህርት ጊዜ እንዲያብራሩ በማድረግ ተሳትፏቸዉን እንዲጨምሩ ማድረግ ነዉ፡፡*
- *ተማሪዎች ከተወያዩ/ ከሰሩ በኋላ ያቀረቡት አንኳር ነጥብ በሳሌዳ ላይ መፃፍ፡፡*
- *የትምህርቱና ይዘት ከአከባቢያቸዉ ጋር በማያያዝ እና በመርጃ መሣርያ በመጠቀም የእለቱን ትምህርት መተንተንእና መመዘን፡፡*

***ሐ.በማጠቃልያ የሚከናዉኑ ድርጊቶች***

- *የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ስኬትን ለማረጋገጥ የክፍል ስራ፣የቤት ስራ፣ፕሮጀክት እና የመሳሰሉትን በቡድን፣በጥንድ እና በግል እንዲሰሩ ማድረግ፡፡*
- *የክፍል ስራ እና የቤት ስራ ለሰሩ ተማሪዎች የሚያስፈልጉትን ግብረ-መልስ መስጠት፡፡*
- *የክፍል ስራ፣ የቤት ስራ፣ፕሮጀክት እና የመሳሰሉት ተሰጥቷአቸዉ መመለስ ላልቻሉት ተማሪዎች የተለየ እገዛ አድርግ/ጊ፡፡*
- *ተማርዎችህ/ሽ የሚቀጥለዉን ትምህርት አንብቦ እንድመጡ ምራቸዉ፡፡*

***መ. ትምህርቱን ዕቅድ ከማቀድ በፊት***

*በመማር እና ማስተማር ሂደት ዉስጥ የስነ ጥበብ መምህራን የትምህርቱን ይዘት ግንዛቤ ለማስጨበጥ እንዲሁም ሙያቸዉን ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻል አለባቸዉ፡፡ ማንኛዉም የተማረ ሰዉ፤የማያነብ/የማይለማመድ ከሆነ የሚያስተምረዉን ትምህርት መርሳቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ይህን ክፍል የሚያስተምሩ የስነ ጥበባት መምህራን የሚከተለዉን የስራ ድርሻ እና ሃላፊነት ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለባቸዉ፡፡*

- *ለዕለቱ የታቀደ የትምህርት ይዘት ወይም ለማስተማር የተዘጋጀዉን በደንብ ማንበብ እና መገንዘብ፡፡*

- ከተማሪዎች መፅሐፍ ለማስተማር የታቀዱትን ትምህርት ጋር የተያያዘዉን እጭር ማስታወሻ መፃፍ፡፡
- ለዕለቱ ትምህርት በተማሪዎች መፅሐፍ የተገለፁት በቂ ካልሆነ፣ ከ5-8 ክፍል ለሚያስተምሩ የስነ ጥበብ መምህራን የተዘጋጀ ማኑዋል ወይም ከተለያዩ የዋቢ መፅሐፎችን ማቀናጀት፡፡
- በተማሪዎች መፅሐፍ ዉስጥ የሚገኙ ሙከራዎች፣ድርጊቶች፣መልመጃዎች እና የክለሳ ጥያቄዎችን ቀድመዉ መስራት፣መሞከር እና መለማመድ አስፈላጊ ነዉ፡፡

# ምዕራፍ 1 የሥነ-ጥበባት ግንዛቤዎች

## 1. የስነ-ጥበባት አይነቶችን መለየትና መግለፅ

### 1.1 የሙዚቃ ኖታዎች

*ለዚህ ምዕራፍ ትምህርት የተሰመጠ አጠቃላይ ክፍለ ጊዜ--25*

***ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የትምህርት ዉጤቶች፡፡***

***ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-***

- ስለሙዚቃ ኖታዎች፣መሠረታዊ ቀለማት፣ፎቶ የማንሳት ዘዴ እና ዲራማ ይረዳሉ፡፡
- ቀላላ በሆነ ምት ተፃፉት የሙዚቃ መሣሪያዎች በመጫወት በተግባር ማሳየት ይችላሉ፡፡
- ቤተሰቦቻቸዉ የሚሰሩት ሥራዎች እንደ ምሳሌ በመዉሰድ፤በመዝሙር፣በዉዝዋዜ፣በማስመሰል እና ድርሻቸዉን በመጫወት ማሳየት ይቾችላሉ፡፡
- ንድፍ፣የቀለም ድብልቅ እና ህትመትን በተግባር ማሳየት ይችላሉ፡፡
- የአከባቢያቸዉን ባህል በሥነ-ጥበባት መንገድ በማስተያየት ያስተዉላሉ፡፡
- ታዋቂ ባሕላዊ እና ዘመናዊ መዝሙሮች እና ዉዝዋዜዎች ይለያሉ፡፡
- በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች እና ቤተ-መዘከር (ሙዚዬም) በማየት ይረዳሉ፡፡
- የሃገራችን ጥበብ ሥራዎች በመዝሙር፣በሥዕል፣በዉዝዋዜ እና የተለያዩ ሚና በመጫወት ይደነቃሉ፡፡

**ሀ. የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች:**

1.1 የሙዚቃ ኖታዎች ---------------( 8 ክፍለ ጊዜ)

1.2 መሠረታዊ ቀለማት ---------------(8 ክፍለ ጊዜ)

1.3 የፎቶ ዘነሳስ ዘዴ እና የዲራማ ጫወታዎች --------------(9 ክፍለ ጊዜ)

# መግቢያ

## ለ. የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ጉብኝት
- የግል እና የጋራ ማብራሪያ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

## ሐ.የትምህርት መርጃ መሣርያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-

- ተለያዩ ፎቶዎች
- የቪዲዮ መጫወቻ
- የተለያዩ ቀለማት
- የሚለማመዱበት ክፍል
- እርሳስ፣ የክራዎን እርሳስ እና በአከባቢ የሚገኙ ንድፍ የሚሰራበቸዉ ነገሮች፡፡
- የተለያዩ ሥዕሎች

## መ. መማር ማስተማርን ማነቃቃት

- ተማሪዎች የተለያዩ ስነ-ጥበባት ለምሳሌ፡- ሥነ-ሥዕል፣ሥነ-ትያትር፣ሙዚቃ እና ዉዝዋዜ መሆኑን በመንገር ምዕራፉን ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ይህን ሥነ-ጥበባትን እንዲለማመዱ አድርጓቸዉ/ጊያቸዉ፡፡ የልምምዳቸዉን ዉጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡

## ሠ.ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ገለፃ

- የክፍል ልምምዶች
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቄ
- ፖርትፎሊዮ
- የሙከራ ጥያቄ
- ፈተና

## 1.1የሙዚቃ ኖታዎች

*ለዚህ ምዕራፍ ትምህርት የተሰመጠ አጠቃላይ ክፍለ ጊዜ--8*

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡

*ከዚህ  ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- ሩብ ኖታ በማንበብ ይጫወታሉ፡፡
- የሩብ ኖታ ቅርጽ በመሳል ያሳያሉ፡፡
- በሩብ ኖታ የተፃፉ ቀላል ምቶችን በማንበብ ይጫወታሉ፡፡

### መግቢያ

ሙዚቃ የራሱ ሆነ ሣይንስ እና ምልክት ያለዉ ትምህርት ነዉ፡፡ ባለፉት ጊዜ ሙዚቃ ከሰዉ ልጅ አኗኗር ጋር ትስስር እንዳለዉ እና የሕብረተሰብን ባሕል እንደሚያንፀባርቅ ተምራቿል፤ አሁንም በመቀጠል ስለ ኖታዎች፣የሙዚቃ ታሪክ፣ባሕል እና ከተለያዩ ትምህርቶች ጋር ግኙነት እንዳለዉ ትማራላችሁ፡፡

## የምዕራፉ አንኳር ነጥቦች

- **የሙዚቃ ኖታዎች**

### *የትምህርት መርጃ መሣርያዎች*

1. ፍላሽ ካርድ
2. ከበሮ
3. ኪቦርድ/ ፒያኖ/ ጊታር
4. የባሕላዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች፤ክራር/መስንቆ እና የመሣሰሉት፡፡
5. ከበላ
6. መረከሽ/ፅናፅል

## *ተከታታይ ምዘና*

የተከታታይ ምዘና ሂደት መከታተል/ በየቀኑ ሚያሳዩትን ለዉጥ መሰረት በማድረግ ግብረ-መልስ በመስጠት እና የተሻለ ዉጤት እየመዘገቡ መሄድ፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

- የዕለት ርዕስ እና የትምህርት ብቃት ለተማሪዎች በማስረዳት፤የግንዛቤ ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያይተዉ እርስበርሳቸዉን በማስተዋውሱ እንዲያስረዱ አድርግ/ጊ፡፡
- የሩብ ኖታ ቅርፅ እና የኖታ ዋጋ በመግለጥ፣በማንበብ እንዲጫወቱ በግል በመለማመድ፣ወደ ቡድን ልምምድ በማሸጋገር ተራበተራ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡

### 1.1.1 ሩብ ኖታ

## የመምህር/ርት ድርሻ

ከዚህ በታች ያሉትን ተማሪዎችን ለማስታወስ መጠየቅ ያለባቸዉ የግንዛቤ ጥያቄዎች በመጠየቅ ጀምር፡፡

1. ሙሉ ኖታ እና ግማሽ ኖታ ምን ይመስላሉ ?
2. እያንዳንዱ ኖታ ስንት የምት ዋጋ አላቸዉ?
3. ሙሉ ኖታ እና ግማሽ ኖታ እንዴት እንጫወታለን?

መምህር/ርት ለግንዛቤ ጥያቄዎች መልሱን ቀድመዉ በተማሩበት ሁኔታ በመግለፅ፤ በመቀጠል ደግሞ አዲሱን ርዕስ ስለ ሩብ ኖታ ማስተማር ነዉ፡፡

ሩብ ኖታ እንደ ግማሽ ኖታ የሙዚቃ ምልክት ሆኖ፤ አንድ (1) የምት ዋጋ አለዉ፡፡ ቅርፁም ከግማሽ ኖታ ጋር ተመሳሳይ ነዉ፡፡ ነገር ግን ራሱ የተቀባ ነዉ፡፡

**የሩብ ኖታ ቅርጽ**




**ይህን ድርጊት በቡድን ከሠሩ በኃላ፤ ተራ በተራ እንዲያስተምሩ አድርጉ፡፡**

1. ሶስት የሩብ ኖታ በመሳል አሳዩ!
2. የሩብ ኖታ ምት ዋጋ ስንት ነዉ?
3. ሩብ ኖታ እንዴት መጫወት ይቻላል ብለህ ታስባለህ?

ከዚህ በታች የተገለፀዉን ሩብ ኖታ እየተጫወቱ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡

ሩብ ኖታ አንድ (1) የምት ዋጋ አለዉ፡፡ ስለዚህ እጃችን አንድ ጊዜ ብቻ በጨብጭበ "'Ta'.." ብለን እንጫወታለን፡፡


ለምሳሌ:






**ልምምድ**

**ሩብ ኖታ እጅ በማጨብጨብ፤ እያነበቡ መጫወት፡፡**

**የተፃፉትን ኖታዎች እንዲለማመዱ ፤ በተለያየ ክፍል ጊዜ በማከፋፈል መረዳታቸዉን ላይ በመመሥረት ቀድመዉ የተረዳ/ዳች ተማሪ ፤ ሠፊ እና ምቹ ጊዜ በመፍጠር ሌሎችን እንዲያስረዱ ማድረግ ነዉ፡፡**

1. 


2. 



3. 

**ሩብ እና ግማሽ ኖታ በማደባለቅ እናማንበብ መጫወት፡፡**





1.


2.





3.




4.



5.



6.



### 1.1.2 ሩብ ምዕራፍ

*ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡*

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **ሩብ ምዕራፍ በማንበብ ያሳያሉ።**
- **ሩብ ምዕራፍ እና ሌሎችን ይለያሉ።**

## የትምህርት መርጃ መሣርያ

- ከበሮ፣ ኪቦርድ/ ፒያኖ
- ባሕላዊ የሙዚቃ መሣርያዎች፤ ክራር/መስንቆ
- ከበላ/መረከሽ/ፅናፅል

## ተከታታይ ምዘና

- የተከታታይ ምዘና ሂደት መከታተል/ በየቀኑ ሚያሳዩትን ለዉጥ መሰረት በማድረግ ፤ ግብረ-መልስ በመስጠት እና የተሸለ ዉጤት እየመዘገቡ መሄድ፡፡

## የመማር እና ማስተማር ዘዴ

ቀድመዉ እያሳዩ የማለማመድ ጥቅም ተማሪዎችን እንደየደረጃቸዉ በመለየት አስፈላጊ በሆነ መንገድ መርዳት፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

- የትምህርቱ ርዕስ እና ዓላማ በመግለፅ፤ ለመነሻ የተቀመጠ ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን በቡድን ተወያይተዉ እንዲነግሩ በማድረግ አስጀምር/ሪ፡፡
- ስለ ሩብ ምዕራፍ ቅርፅ እና ያለዉን የምት ዋጋ፤ቀድመዉ እያሳዩ የማለማመድ፤የሚቀጥለዉን ላምምድ ቀስ በቀስ እየተጫወቱ እንዲማሩ አድርግ/ጊ፡፡

**የሚከተሉትን የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጀምር/ሪ**

1. ግማሽ ምዕራፍ ምን እንደሚመስል ታስታዉሳለህ? ብለህ/ሽ ጠይቅ/ቂ፡፡


2. ግማሽ ምዕራፍ ምልክት በመሳል ፤እንዴት አንብበዉ እንደሚጫወቱ ለጓደኞቻቸዉ እንዲያሳዩ አድርጉ፡፡

የተጠየቁትን የግንዛቤ ጥያቄዎች መልስ በተማሩት ሁኔት እንዲገልፁ፤በሚከተለዉ ተጨማሪ ማስታወሻ ስጧቸዉ፡፡

የሩብ ምዕራፍ የምት ዋጋ ከሩብ ኖታ ጋር እኩል ዋጋ አላቸዉ፡፡ ልዩነታቸዉ ድምፅ መኖራቸዉ እና አለመኖራቸዉ ነዉ፡፡ ሩብ ኖታ ሲንጫወት ድምፅ አለዉ ሩብ ምዕራፍ ደግሞ ድምፅ የለዉም ዝም ብለን እንጫወታለን፡፡ ሩብ ምዕራፍ ምልክት የሚከተለዉ በማየት ለጓደኞቻቸዉ እንዲያሳዩ አድርግ/ጊ፡፡




ሩብ ምዕራፍ እያነበቡ እንዲለማመዱ ቀድመህ አንተ/አንቺ አሳያቸዉ/ይኳቸዉ




**የሙዚቃ ኖታዎች ንባብ ልምምድ**

***መምህር/ርት***


ከዚህ በታች ያሉትን ኖታዎች፤ ምዕራፍ ባለበት ቦታ ዝም በማለት፤ ድምፅ ባላቸዉ ቦታ ደግሞ “Taa” የሚል ድምፅ በማሰማት፤ እጃችን እያጨበጨቡ የምት ዋጋቸዉን እየቆጠሩ እንዲጫወቱ አድርግ/ጊ፡፡

1. 


2.



3.



4.





5.



6.



7. 

8. 

## 1.2 መሠረታዊ ቀለማት

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ አጠቃላይ የትምህርት ክፍለ ጊዜ…..8

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **በአከባቢያቸዉ የሚገኙ ቀለማት በመገነዘብ ይለያሉ፡፡**
- **የመሠረት ቀለም ይፅፋሉ፡፡**
- **በመሠረት ቀለም ፤ የቀለም ቅብ በመሥራት ያሳያሉ፡፡**

## አንኳር ነጥብ

- *መሠረታዊ ቀለም/ ንጥረ ቀለም*

**ቅድመ ዝግጅት**

ይህን ርዕስ ለማስተማር የዕለቱን ትምህርት ዕቅድ ካዘጋጀህ በኋላ ከዚህ ይዘት ጋር የሚሄድ የትምህርት መርጃ መሳርያ፤ የንጥረ ቀለም ቻርት እና ቀለም ይዘዉ መምጣት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ጉብኝት
- የግል እና የጋራ ማብራሪያ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

### የትምህርት መርጃ መሣርያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-

- ተለያዩ ፎቶዎች በመሠረታዊ ቀለም ማሳየት፡፡
- በመሠረታዊ ቀለም እና የቀለም ቻርት ሥዕል፡፡
- የሚለማመዱበት ክፍል
- እርሳስ እና የከራዎን እርሳስ፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

በዚህ ትምህርት ይዘት ለተማሪዎች በቂ ማብራሪያ በመሥጠት፣ ቶሎ ተምረዉ ተጨማሪ ተግባር ለመሥጠት እንዳይሰለቻቸዉ አድርግ/ጊ፡፡

መሠረታዊ ቀለም ለሁሉም ቀለም መሠረት ነዉ፡፡ ይህም መሠረታዊ ቀለም እንደ ሌሎች ቀለም በመቀየጥ ማግኘት አንችልም፣ ነገር ግን ተራ በተራ በመቀየጥ ሌሎቸችን ቀለማት ማግኘት እንችላለን፡፡ እነዚህም ቀለሞች አንደኛ ደረጃ (ሰዉ ሰራሽ መሠረታዊ ቀለም) ቀለም በመባል ይጠራሉ፡፡ሦስት መሰረታዊ ቀለሞች አሉ እነዚህም፡-ቀይ፣ቢጫ እና ሠማያዊ ናቸዉ፡፡

በዝግታ የሚረዱ ተማሪዎች ደግሞ በእረፍት ጊዜ ከሌሎች ጋር እኩል እንዲሆኑ እርዳቸዉ፡፡

### ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ገለፃ
- የክፍል ልምምዶች
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቄ

## 1.2.1. የመሠረታዊ ቀለማት አይነቶች

*ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡*

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- መሠረታዊ ቀለማት ይለያሉ፡፡
- የመሠረት ቀለም አይነቶችን ይፅፋሉ፡፡
- የመሠረት ቀለም አደበላለቅ ይለማመዳሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- የግል እና የጋራ ማብራሪያ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

## የትምህርት መርጃ መሣርያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣሪያዎች፡-

- ተለያዩ ፎቶዎች በመሠረታዊ ቀለም ማሳየት፡፡
- በመሠረታዊ ቀለም እና የቀለም ቻርት ሥዕል፡፡
- የሚለማመዱበት ክፍል
- እርሳስ እና የከራዎን እርሳስ፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

መምህር/ርት፤በመጀመሪያ የመሠረታዊ ቀለም ምንነት የአዕዋፋት መልክ፣ የቤት እንስሳት እና አበባ ከተማሪዎች መፅሐፍ ሥዕል 1.1. መሰረት በማድረግ ግለፅ/ጪ፡፡ በመቀጠል መሠረታዊ ቀለም ምን እንደሆኑ ምሳሌ በመጥቀስ ግለፅ/ጪ፡፡ ከዚያ በኋላ ተማሪዎች የተረዱትን እንዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡ በዚህ ሂደት የመሠረታዊ ቀለም ተረድተዉ መለየታቸዉን በመከታተል ግብረ መልስ ሥጥ/ጪ፡፡

በአከባቢያቸዉ የሚገኙትን ቀለማት የሚያዉቁ ከሆነ ፤ ወይም ቤተ ሰቦቻቸዉን በመጠየቅ ክፍል ዉስጥ እንዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡ በመጨረሻ ደግሞ በዚህ ምዕራፍ ተሰጡትን መልመጃዎች በማሰራት፤መረዳታቸዉን በማረጋገጥ ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

## . ልምምድ 1. የአበባ ንድፍ መንደፍ

**በመልመጃ 1 ተማሪዎች ከተማሪ መፅሐፍ የአበባ ንድፍን በወረቀት ላይ ከሳሉ በኋላ፤ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ።**

- ከተማሪ መፅሐፍ የአበባ ንድፍን በወረቀት ላይ እንዲነድፉ አድርግ/ጊ፡፡
- በተማሪ መፅሐፍ ላይ የተሰጠ የአበባ ሥዕል በመሳሉ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡
- ካለማመድካቸዉ/ሽዉ በኋላ ሌሎች ሥዕል እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡

መምህር/ርት ተማሪዎች ከዚህ ከአበባ ንድፍ ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡ ለምሳሌ፤- መጀመሪያ ላይ ያለዉ የአበባ ቀለም ቢጫ፣ብርቱካናማ እና አረንጓዴ መሆኑና ከትምህርት ቤት መልስ ቤተሰቦቻቸዉ እንዴት እንደሚያስረዳቸዉ የተለያዩ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያለዉን ሥዕሎችን እንደሚያሳዩ እና የመሳሰሉትን አስረዳ/ጂ፡፡

### መልመጃ 2 የወፍ ንድፍ በመንደፍ ቀለም መቀባት

**በመልመጃ 2 ፡ ተማሪዎች ከተማሪ መፅሐፍ የወፍ ንድፍን በወረቀት ላይ ከሳሉ በኋላ፤ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ።**

### የመምህር/ርት ድርሻ

- ተማርዎች የዚህን መልመጃ ትዕዛዝ በመከተል የንድፎችን ቅድመተከተላቸዉን በመጠበቅ እንዲስሉ አበረታታቸዉ፡፤
- በመልመጃ 2 የተሰጠ የወፍ ንድፍን ተለማምደዉ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡
- በመልመጃ 2 የተሰጠ የወፍ ንድፍን ካለማመድካቸዉ በኋላ ሌሎች ንድፍ

እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡

- በመጨረሻም በየግላቸዉ የሰሩትን፤ በቡድን እንዲወያዩ አድርግ/ጊ፡፡
- መምህር/ርት ተማሪዎች ከዚህ ከአበባ ንድፍ ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡ ለምሳሌ፤-በወፍ ሥዕል ላይ ያለዉ ቀለም ቢጫ፣ሠማያዊ፣ጥቁር መሆንና ሌሎች በአከባቢያቸዉ ከሚገኙት ወፍ ምን አይነት ቀለም እንደሚገኝ በመለየት እንዲነግሩ  አድርግ/ጊ፡፡

ከትምህርት ቤት መልስ ቤተሰቦቻቸዉ እንዴት እንደሚያስረዳቸዉ የተለያዩ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያለዉን ሥዕሎችን እንደሚያሳዩ እና የመሳሰሉትን አስረዳ/ጂ፡፡

## መልመጃ 3 የወፍ ንድፍ

**በመልመጃ 3 ፡ተማሪዎች ከተማሪ መፅሐፍ የወፍ ንድፍን በወረቀት ላይ ከሳሉ በኋላ፤ቀለም እንዲቀቡ  አድርግ/ጊ።**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- ተማርዎች የዚህን መልመጃ ትዕዛዝ በመከተል ንድፎችን ቅድመተከተላቸዉን በመጠበቅ እንዲስሉ አበረታታቸዉ፡፤
- በመልመጃ 2 የተሰጠ  የወፍ ንድፍን ተለማምደዉ ቀለም እንዲቀቡ  አድርግ/ጊ፡፡
- በመልመጃ 2 የተሰጠ  የወፍ ንድፍን ካለማመድካቸዉ በኋላ ሌሎች  ንድፍ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡
- በመጨረሻም በየግላቸዉ የሰሩትን፤ በቡድን እንዲወያዩ አድርግ/ጊ፡፡

መምህር/ርት ተማሪዎች ከዚህ ከአበባ ንድፍ ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡ ለምሳሌ፤- በወፍ ሥዕል ላይ ያለዉ ቀለም ቀይ፣አረንጓዴ፣ደብዛዛ ቡኒ እና አረንጓዴ ዉሃማ መሆንና ሌሎች በአከባቢያቸዉ ከሚገኙት ወፍ ምን አይነት ቀለም እንደሚገኝ እንዲነግሩ  አድርግ/ጊ፡፡

ከትምህርት ቤት መልስ ቤተሰቦቻቸዉ እንዴት እንደሚያስረዳቸዉ የተለያዩ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያለዉን ሥዕሎችን እንደሚያሳዩ እና የመሳሰሉትን አስረዳ/ጂ፡፡

**መልመጃ 4. የአዉሮፕለን ንድፍ በመንደፍ ቀለም መቀባት**

**በመልመጃ 4፡ተማሪዎች ከተማሪ መጥሐፍ የአዉሮፕለን ንድፍን በወረቀት ላይ ከሳሉ በኋላ፤ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ።**

- ተማርዎች የዚህን መልመጃ ትዕዛዝ በመከተል፤ የአዉሮፕለን ንድፍ ቅድመተከተላቸዉን በመጠበቅ ፤ለሥዕል ባዘጋጁት ወረቀት ላይ እንዲስሉ አበረታታቸዉ፡፡
- በአዉሮፕለን ላይ ያለዉን ቀለማት ከተነጋገሩ በኃላ፤ እያንዳንዳቸዉ ተነስተዉ እንዲነግሩ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች በአዉሮፕለን ላይ ያለዉን ቀለማት መለየታቸዉን በመከታተል አረጋግጥ፡፡
- በመጨረሻም የሳሉትን የአዉሮፕለን ንድፍ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

**መልመጃ 5 የዝንጀሮ ንድፍ በመንደፍ ቀለም መቀባት**

**በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ከተማሪ መጥሐፍ የዝንጀሮ ንድፍን በወረቀት ላይ ከሳሉ በኋላ፤ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ።**

**የመምህር/ርት ድርሻ**

- ተማርዎች የዚህን መልመጃ ትዕዛዝ በመከተል፤ የዝንጀሮ ንድፍ ቅድመተከተላቸዉን በመጠበቅ ፤ለሥዕል ባዘጋጁት ወረቀት ላይ እንዲስሉ አበረታታቸዉ፡፡

- የእርስበርሳቸዉን ንድፍ በማየት መሳል መቻላቸዉን ማን በደንብ እንደሳሌ ተራ በተራ ተነስተዉ እንዲያብራሩ አድርግ/ጊ፡፡
- ይህን ንድፍ መሳል የቻሉትን ተማሪዎች በመመልከት አረጋግጥ/ጪ፡፡
- በየግላቸዉ የሰሩትን፣ በቡድን እንዲወያዩ አድርግ/ጊ፡፡
- በመጨረሻም የእርስ በርሳቸዉን ማስተካከላቸዉን ካረጋገጥክ/ሽ በኋላ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

**መልመጃ 6. የመኪና ንድፍ በመንደፍ ቀለም መቀባት**

**በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ከተማሪ መጥሐፍ የመኪና ንድፍን በወረቀት ላይ ከሳሉ በኋላ፤ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ።**

**የመምህር/ርት ድርሻ**

- ተማርዎች የዚህን መልመጃ ትዕዛዝ በመከተል፣ የመኪና ንድፍ ቅድመተከተላቸዉን በመጠበቅ ፣ለሥዕል ባዘጋጁት ወረቀት ላይ እንዲስሉ አበረታታቸዉ፡፡
- በመኪና ላይ ያለዉን ቀለማት ከተነጋገሩ በኃላ፣ እያንዳንዳቸዉ ተነስተዉ እንዲነግሩ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች በመኪና ላይ ያለዉን ቀለማት መለየታቸዉን በመከታተል አረጋግጥ፡፡
- በመጨረሻም የሳሉትን የመኪና ንድፍ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

መምህር/ርት ተማሪዎች ከዚህ ምዕርፍ ሥር ያሉት መሠረታዊ ቀለሞች ምን እንደተረዱ በመጠየቅ ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡ ለምሳሌ፡- መሠረታዊ ቀለሞችን በመለየት መቀባታቸዉን በማረጋገጥ፣ ከትምህርት ቤት መልስ ቤተሰቦቻቸዉ ስለ መሠረታዊ ቀለሞች እንዴት እንደሚያስረዳቸዉ እና የተለያዩ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያለዉን ሥዕሎችን እንደሚያሳዩ እና የመሳሰሉትን እንዲለማመዱ በማሳየት አበረታታቱ፡፡

## 1.3 የፎቶ አነሳስ ዘዴ እና የዲራማ ጫወታ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ አጠቃላይ የትምህርት ክፍለ ጊዜ…..12

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **ፎቶ ምን እንደሆነ ይረዳሉ፡፡**
- **የፎቶ አና ሥዕል ልዩነት ይለያሉ፡፡**
- **የትያትር ጫወታ ድግጊቶች በፎቶ እንደሚገለፁ ይረዳሉ፡፡**





## የይዘቱ አንኳር ነጥቦች

- ፎቶ
- የፎቶ መልዕክት
- ፎቶ የማንሳት /ፎቶ ግራፍ
- የዲራማ ጫወታ ማሰራት
- የዲራማ ጫወታ መልዕክት

## የትምህርት መርጃ መሣርያዎች

- ካሜራ
- የሚለማመዱበት ሜዳ
- የተለያዩ ፎቶዎችን የሚመለከቱበት ክፍል

ፎቶግጋፍ ማለት ብርሃንን በመጠቀም ፎቶ ማንሳት ማለት ነዉ፡፡ ከዚህ በታች የሚትመለከቱ መሣርያ ካሜራ ይባላል፡፡





ካሜራ



ትራይፖድ/የካሜራ ተሸካሚ

ፎቶ ግራፍ ከሁለት ቃላቶች የተመሠረተ ነዉ፡፡ እነርሱም፡-ፎቶ ማለት '***ብርሃን*** ሲሆን ግራፍ ደግሞ' ***ማንሣት/መቅረፅ*** ማለት ነዉ፡፡ ስለዚህ ካሜራን በመጠቀም ፎቶ የማንሳት ሂደት ፎቶግራፍ ማለት ነዉ፡፡



ፎቶ ለማንሳት ካሜራ የያዘች ልጅ

መምህር/ርት ከዚህ በታች የሚታዩት ፎቶዎች፤ ካሜራ በመጠቀም የተቀረፁት መሆናቸዉን ለተማሪዎች አስረዳ/ጂ፡፡

ፎቶ ከሥነ-ጥበብ ዉስጥ አንዱ ነዉ፡፡ ፎቶ ማለት ህይወት ያላቸዉና ህይወት የለላቸዉን ነገሮችን የሚናነሳ ነገር ፊትለፊት በማድረግ ካሜራ በመጠቀም የሚንቀርጽ ነዉ፡፡

ስለዚህ የተክኖሎጂ መሣሪያ ሆኖ ፎቶ ለማንሳት የሚያገለግለን **ካሜራ** ይባላል፡፡ ፎቶ ማንሳት የሚንችለዉ ነገሮች ለምሳሌ፡-
ሰዉ፣እንስሳቶች፣እፅዋቶች፣ነፍሳቶች፣ድንጋይ፣ወንዝ፣ሰማይ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ አለም ላይ ያሉ የሚታዩ ነገሮችን ፎቶ ማንሳት እንችላለን፡፡ በማንኛዉም ሁኔታ ወይም አጋጣሚ ፎቶ ማንሳት እንችላለን፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

መምህር ከላይ በተቀመጠ ሁኔታ እና በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የቀረበዉን የካሜራ ምስል ተማሪዎችን አስረዳቸዉ/ጃቸዉ፡፡

ፎቶ ከሥዕል ከልዩ የሚያደርገዉ የካሜራ ብርሃን በመጠቀም እንዲቀረፅ የተፈለገ እንዳለ የሚቀረፅ ሲሆን፤ ሥዕል ደግሞ ሠዓሊዎች ባላቸዉ ችሎታ የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም በወረቀት፣ጨርቅ እና የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም የሚስሉ ነዉ፡፡

## ፎቶ የማንሳት ዘዴዎችን ፃፍላቸዉ

ፎቶ የማንሳት ዘዴዎች ሰባት (7) መሠረታዊ መምሪያ አለዉ፡፡ እነርሱም፡-

- መጠያየቅ
- ምት
- ምስል
- ትኩረት
- የቀለም ምዛን
- አንድነት
- እንቅስቃሴ



የፎቶ ግራፍ መምሪያዎችን በመከተል ፎቶ ግራፈሮች መሠረትዊ የፎቶ ጥበብ አነሳስ ንድፍ ሃሳብ በመከተል ፎቶ የሚቀርመቅረፁበት ሂደት ነዉ፡፡ በመከተልም በመፅሐፋቸዉ ላይ የቀረበዉን ፎቶዎች በካሜራ በመጠቀም እንዲሁም ከላይ የተገለጹት መምሪያ በመከተል የተቀረፁ መሆናቸዉን ንገራቸዉ/ሪያቸዉ፡፡

ከዚያ በኋላ በስልክህ/ ካሜራ ካለ በመጠቀም ተማሪዎች ፎቶ እንዲቀርፁ ጠይቁአቸዉ፡፡ ከቀረጹ በኋላ ክፍል ዉስጥ የቀረጹበት ሂደት እና የተቀረፀ ነገር ምን እንደሆነ በመየቅ ሕፃናት በቀላሉ እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡ ካሜራ ጥቅም ፎቶ ለማንሳት ያገለግላል ለምሳሌ፡- ፓስፐርት፣ የጤና መዝገብ፣የማስታወቂያ ሥራ እና የመሳሰሉት በመቅዳት ለጥበብ ሥራዎች ማዕከል ሊሆን ችሏል፡፡
ስለዚህ ማንኛዉም ሰዉ የተለያዩ መረዳዎችን በመቅረፅ ማስቀመጥ ይችላል፡፡ ከመመሪያ ዉጪ ፎቶ ማንሳት/መቅረጽ የራሱ ባሕርይ አለዉ፡፡

**የፎቶ ግራፍ ዋነኛ ባሕርያት**

- **ብርሃን እና**

- **ጨለማ**

**ፎቶ ማንሳት ሰባት (7) ባህርያት አለዉ፡፡ እነርሱም፡-**

- ቅንጅት
- ብርሃን
- ጎድጋዳማ
- መስመር
- ሸካራነት እና ለስላሳማነት
- ምስል
- ቦታ

በፎቶ ለመግለጽ እንደተሞከረዉ ሰዎችን ወይም የሚቀሳቀሱ ነገሮችን መቅረፅ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ትያትር ዲራማ የሚሰሩ ሰዎች ፎቶ በመቅረጽ ድርጊታቸዉ እና ስሜታቸዉን መግለጽ ይቻላል፡፡

የተቆጣች እናት እና ተዕዛዟን ላለመቀበል ያኮረፌ ልጅ የሚያሳይ ፎቶ፡፡



*በመድረክ ላይ የተለያየ ጫወታዎችን የሚጫወቱ ሕፃናት የሚያሳይ ፎቶ*



## የመምህር/ርት ድርሻ

የትያትር ጫወታ ወይም ከተለያዩ ዲራማ የተወሰዱ ድርጊቱን ዓይተው እንዲለዩ አድርግ/ጊ፡፡ የትያትር ጫወታ የመቅዳት ዋናዉ ዓላም ታሪክን ወይም መልዕክት ማስተላለፍ ነዉ፡፡ ስለዚህ ከዲራማ ድርጊት የተወሰደ ፎቶ ሰዉን የሚስብ መሆን አለበት፡፡ የዲራማ ፎቶዎች በእይታችን ሞራል በመጨመር፤ ጥሩ ግብረ መልስ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ የተለያዩ ኮንሰርት ፎቶዎች፣የዉዝዋዜ ፎቶዎች፣የትያትር ጫወታ ፎቶዎች ሁሉም የመድረክ ሥራዎች ናቸዉ፡፡

መምህር/ርት በሁለተኛ ክፍል የሰሩትን የትያትር ጫወታወች ፎቶ ካለ በማሳየት፤ ዲራማ የተለያዩ ፎቶዎች ወደ ቪዲዮ መቀየር የሚቻል መሆኑን ንገሩአቸዉ፡፡

**መምህር/ርት የትያትር ጫወታ መቅዳት ጥቅሙን ለተማሪዎቻችሁ አስረዱ፡፡**

- የትያትር ጫወታ ፎቶ በማንሳት እንደ መረጃ ማስቀመጥ እና ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ሚና አለዉ፡፡
- የትያትር ጫወታ መቅዳት፤በመድረክ ላይ እየተካሄደ ያለዉ የጥበብ ሥራዎች፣የሚተላለፈዉ መልእክት እና የመቼት ዲዛይን በመቅረፅ አጠራቅሙ፡፡
- የትያትር ድርጊቶች እና ትዕይንቶችን በመቅረጽ ለፖስተር፣ለመፅሔት እና ማስታወቂያ ለመሥራት እንደሚያገለግል ተማሪዎችን አስረዷቸዉ፡፡

***ተከታታይ ምዘና***

- የግል እና ቡድን ገለፃ

- ፖርትፎሊዮ
- ፈተና

በመጨረሻም የተሰጠዉን መልመጃ አሰራ/ሪ፡፡ በተጨማሪ የተለያዩ ጥያቄዎችን አዘጋጅታችሁ በቃል በመጠየቅ ወይም በማሰራት፤የዚህ ምዕራፍ ዓላማ መረዳታቸዉን እስክታረጋግጡ ያለዉን ደካማ ጎን በመለየት ደግመህ/ሽ ሕፃናቶችን አለማምዳቻዉ፡፡

**የመልመጃ 1 መልስ**

**1.ሐሰት**

**2. መ**

**3. ካሜራ ይባላል**

**መልመጃ 2 መልስ**

1. **ተማሪዎች የተለያዩ ፎቶዎችን ይዘዉ ይመጣሉ ብለን እናምናለን፡፡**

# ምዕራፍ 2 ፡ የፈጠራ ችሎታ

## 2. የሥነ ጥበባት ልምምድ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ አጠቃላይ የትምህርት ክፍለ ጊዜ..............27

*ከዚህ ትምህርት ምዕራፍ የሚጠበቁ ዉጤቶች፡*

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

- የፈተራ ችሎታ ምን እንደሆነ ያብራራሉ፡፡
- ንድፍ፣ የቀለም ድብልቅ እና ህትመት በመሥራት ማሳየት ይችላሉ፡፡

### ሀ. የምዕራፉ ዋና  ዋና ይዘቶች:

2.1 የሙዚቃ ድምፆች፣ ኖታዎች እና የምት ሙዚቃ መሣሪያ --------(7 ክፍል ጊዜ)

2.2 ቀላል የሆኑ ቅርፆችን ቀለም መቀባት --------(7 ክፍል ጊዜ)

2.3 የመሠረታዊ ቀለም ድብላቅ እና ቀጥተኛ ህትመት-------(6 ክፍል ጊዜ)

2.4 የዲራማ መልዕክቶች፣ቪዲዮ እና ፎቶ---------(7 ክፍል ጊዜ)

### ለ.የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ጉብኝት
- የግል እና የጋራ ዕብረቃ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

## ሐ.የትምህርት መርጃ መሣሪያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣሪያዎች፡-

- የተለያዩ ፎቶዎች
- የቪዲዮ መጫወቻ
- የተለያዩ ቀለማት
- የሚለማመዱበት ክፍል
- እርሳስ፣ የክራዎን እርሳስ እና በአከባቢ የሚገኙ ንድፍ የሚሰራበቸዉ ነገሮች፡፡
- የዉሃ ቀለም፣ ዉሃ ቀለም ብሩሽ እና በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች፡፡
- የተለያዩ ሥዕሎች

## የመምህር/ርት ድርሻ

መምህር/ርት በመጀመሪያ፤ የፈጠራ ችሎታ ምንነት ካስረዳሃቸዉ በኋላ፤ ተማሪዎች እንዴት ሆነዉ የፈጠራ ችሎታቸዉን እንዲያሳድጉ አብራራላቸዉ፡፡ በአከባቢያቸዉ የሚገኘዉን ነገር ንድፍ በመንደፍ፤ቀለም በመቀባት ችሎታቸዉን እንዲያሳድጉ አድርጓቸዉ፡፡

በተጨማሪ ተማሪዎች በፍላጎታቸዉ መሠረት፤ በአከባቢያቸዉ ከሚገኙ ነገሮች የፈለጉትን ነገር ሥለዉ ቀለም እንዲቀቡ አበረታቱ፡፡ የእያንዳንዳቸዉ ሥራቸዉን በመመዘገብ፤ በጥሩ ሁንታ የሰሩትን በማበረታታት በዝግታ የሚማሩትን ለብቻ ተጨማሪ እገዛ ስጧቸዉ፡፡

## ሠ.ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ገለፃ
- የክፍል ልምምዶች
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቄ
- ፖርትፎሊዮ

- የሙከራ ጥያቄ
- ፈተና

## 2.1 የሙዚቃ ድምፆች፣ኖታዎች እና የምት መዚቃ መሣሪያዎች

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ------------------7

### 2.1.1 የሙዚቃ ድምፆች

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **የሙዚቃ ድምፃችን ይፅፋሉ፡፡**
- **የሙዚቃ ኖታዎች እና ምዕራፎቹን ይጫወታሉ፡፡**

### የሙዚቃ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

- ከበሮ፣ትንሹ ኪቦርድ፣ፒያኖ እና ጊታር፡፡
- ባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያ፣ክራር እና መስንቆ፡፡
- ከበላ፣መረከሽ እና ፅናጽል

### ተከታታይ ምዘና

☞ የተከታታይ ምዘና ሂደት መከታተል፣ ዕለት በዕት የሚያሳዩ ለዉጥ በማየት ግብረ መልስ መስጠት እና የተሸለ ነጥባቸዉን መመዝገብ፡፡

### የመማር እና ማስተማር ዘዴዎች

ቀድመዉ በማሳየት ማስተማር

### የመምህር/ርት ድርሻ

- የዕለቱን ርዕስ እና ዓላማ በማስተዋወቅ፤ የሚያቁትን ነገር ማዕከል በማድረግ የተዘጋጀዉን የግንዛቤ ጥያቄዎች በቡድን ተወያተዉ ሃሳባቸዉን እንዲገልፁ አድርግ/ጊ፡፡
- ታዋቂ የሙዚቃ ድምፆች ምን እንደሆኑ እና ድምፃቸዉ እንዴት እንደሆኑ ቀድመዉ በማሳየት እና በማሰማት "Doo ree mii……" በቀላሉ እንዲዘምሩ አድርግ/ጊ፡፡ ለዚህ ደግሞ ትንሹ ኪቦርድ ወይም በሞባይል ላይ የኪቦርድ ሶፍትውር በመጫን መጠቀም ይቻላል፡፡.

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡

1. ከሙዚቃ ድምፆች የቱን ታዉቃላችሁ? በምሳሌ ግለጥ/ጪ፡፡
2. አዕዋፋት ሲያዜሙ ሰምተህ/ሽ ታዉቃለህ/ሽ? እንዴት ይላሉ ?
3. ሰዉ የሙዚቃ ድምፅ አስመስለዉ ማዜም ይችላል ?
4. የሙዚቃ መሣሪያ ሲጫወቱ አይተህ/ሽ ታዉቃለሽ? ድምፁ እንዴት ነዉ ?

**መልስ**

የሰዉ ልጅ ከጥንት ዘመን ጀምረዉ በድምፁ በማዜም እና በባሕላዊ ሙዚቃ እና ድምፆችን በመጠቀም ነበር፡፡

**ሰባቱ** (7) በዘመናዊ የሙዚቃ ድምፆች መልክ የሚባሉ፡-

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| "Doo | Ree | Mii | Faa | Sool | Laa | Sii | Doo" |
| C | D | E | F | G | A | B | C |

በፒያኖ ወይም ኪቦርድ ቁልፎቹ ካሉ፤ መጫወት እንችላለን፡፡ የማናገኝ ከሆነ ደግሞ በሞባይል ላይ መጫወት የሚንችለዉ ቁልፎችን ከእንተርኔት በማዉረድ ድምፁን እንዲሰሙ ማድረግ ነዉ፡፡.

Doo Ree Mii Faa Sool Laa Sii Doo

## 2.1.2 ኖታዎች

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **ሙሉ ኖታ፣ ግማሽኖታ እና ሩብ ኖታ በማስታወስ ተጫዉተዉ ያሳያሉ፡፡**
- **የሙሉ እና ግማሽ ኖታ ዋጋ ይለያሉ፡፡**

## አንኳር ነጥቦች

- ኖታዎች

## የትምህርት መርጃ መሣሪያ

ከበሮ፣ካባላ፣መረከሸ፣ትንሹ ኪቦርድ እና የመለማመጃ ሜዳ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ቀድመዉ በማሳየት ማስተማር

### ተከታታይ ምዘና

- የተከታታይ ምዘና ሂደት በመከታተል ዕለት በዕት የሚያሳዩ ለዉጥ በማየት ግብረ መልስ መስጠት እና የተሸሉ ነጥባቸዉን መመዝገብ፡፡

### የመምህር/ርት ድርሻ

- የዕለቱን ርዕስ እና ዓላማ በማስተዋወቅ፣ የተዘጋጀዉን የግንዛቤ ጥያቄዎች እንዲሰሩ አድርግ/ጊ፡፡
- የቅርፅ ምንነት እና ኖታዎች ያላቸዉ የምት ዋጋ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ካለዉ ጋር በማስተዋወቅ፣ ቀጥለዉ ያለዉ ልምምድ በግል እና ቡድን ተለማምደዉ እነዲያሳዩ አድርግ/ጊ፡፡


የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻዉ ጋር በመሥራት፤ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡

1. ኖታ ምንድነዉ?
2. ኖታ ለምን ይጠቅማል ?
3. ምን አይነት ኖታ ተማርክ/ሽ ?


**መልስ**

ኖታ የሙዚቃ ፊደል ሆኖ፤ ምት እና ዜማ እንዴት እንደሚፃፍ ማስረዳት፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ኖታዎች እንዳሉ የሚከተለዉን ማሳሌ በመዉሰድ አስረዳ/ጂ፡፡

1. **.ሙሉ ኖታ፡** ክብ የሚመስል እና የምት ዋጋዉ አራት (4) ነዉ፡፡ ቅርጹም የሚከተለዉን ይመስላል፡፡



2. **.ግማሽ ኖታ፡** ሙሉ ኖታ የሚመስል ሆኖ፣ ከራስ ላይ አጭር ግንድ ያለዉና ያልተቀባ ሲሆን የምት ዋጋዉ ሁለት (2) ነዉ፡፡ ቅርጹ ደግሞ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡



**ሩብ ኖታ፡** ደግሞ ግማሽ ኖታ የሚመስል ሆኖ፤ራሱ የተቀባ ሲሆን የምት ዋጋዉ አንድ (1) ነዉ፡፡

ቅርፁም ሚከተለዉን ይመስላል፡



# 2.1.3 እርፍት

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **የተለያዩ እረፍቶችን ይለያሉ፡፡**
- **እረፍቶችን አንብበዉ በመጫወት ያሳያሉ፡፡**
- **የእረፍቶች አይነት ይፅፋሉ፡፡**

**አንኳር ነጥብ**

- እረፍቶች

## የትምህርት መርጃ መሣሪያ

ከበሮ፣ካባላ፣መረከሸ፣ትንሹ ኪቦርድ እና የመለማመጃ ክፍል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ቀድመዉ በማሳየት ማስተማር

### ተከታታይ ምዘና

- የተከታታይ ምዘና ሂደት መከታተል፣ዕለት በዕት የሚያሳዩ ለዉጥ በማየት ግብረ መልስ መስጠት እና የተሻለ ነጥባቸዉን መመዝገብ፡፡

### የመምህር/ርት ድርሻ

- የዕለቱን ርዕስ እና ዓላማ በማስተዋወቅ፣ የተዘጋጀዉን የግንዛቤ ጥያቄዎች እንዲሰሩ አድርግ/ጊ፡፡

- የቅርፅ ምንነት እና እረፍቶች ያላቸዉ የምት ዋጋ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ካለዉ ጋር በማስተዋወቅ፣ ቀጥለዉ ያለዉ ልምምድ በግል እና በቡድን ተለማምደዉ እነዲያሳዩ አድርግ/ጊ፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ከጓደኞቻተዉ ጋር እንዲሰሩ አመቻች/ቺ፡፡

1. የኖታ ዕረፍት ምንድነዉ ?
2. የኖታ ዕረፍት ለምን ይጠቅማል?
3. ምን አይነት የኖታ ዕረፍት ተማርክ/ሽ ?

**መልስ**: በሚከተሉት ሁኔታ በማስረዳት አስተምር/ሪ፡፡

እረፍት የሙዚቃ ፊደል ሲሆን፣ የምት ፅሑፍ እና ዜማ ዋጋቸዉ የሚተመንበት ቦታ ዝም በማለት ይታለፋል፡፡

የእረፍት አይነቶች:

1.**ሙሉ እረፍት፡** የቆይታ ምት ዋጋ አራት (4) ያለዉና፣ቅርጹ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡



2..**ግማሽ እረፍት**፡ የቆይታ ምት ዋጋ ሁለት (2) ያለዉና፣ቅርጹ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡



3.**ሩብ እረፍት፡** የቆይታ ምት ዋጋ ሁለት (2) ያለዉና፣


ቅርጹ የሚከተለዉን ይመስላል፡፡




**ድርጊት**

ከዚህ በታች የተፃፉት ኖታዎች በግል እንዲለማመዱ በማድረግ፣ በቡድን እጅ በማጨብጨብ ወይም ከበሮ በመምታት አብረዉ እያነበቡ እንዲጫወቱ አመቻች/ቺ፡፡


1.



2.



3.



4.



5.



## 2.1.4 የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **ባሕላዊ የምት ሙዚቃ መሣሪያ ፃፍ፡፡**
- **በአከባቢያችሁ የሚገኝ የምት ሙዚቃ መሣሪያ ሥዕል በመሳል ያሳያሉ፡፡**

**አንኳር ነጥብ**

- *የምት ሙዚቃ መሣሪያ*

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ ብዛት-----------2

### የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- የከበሮ፣ካባላ፣መረከሽ፣ትንሹ ኪቦርድ እና የመለማመጃ ክፍል፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ቀድመዉ በማሳየት ማስተማር
- የቡድን ዉይይት
- መጠይቅ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ

### ተከታታይ ምዘና

የተከታታይ ምዘና ሂደት መከታተል፣ዕለት በዕለት የሚያሳዩ ለዉጥ በማየት ግብረ መልስ መስጠት እና የተሻለ ነጥባቸዉን መመዝገብ፡፡

### የመምህር/ርት ድርሻ

- የእለቱን ርዕስ እና ዓላማ አስተዋዉቅ/ቂ፡፡

- የአከባቢያቸዉ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች እንዲፅፉ አድርግ/ጊ፡፡
- የአከባቢያቸዉ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች እንዲሥሉ በማድረግ፣ ነጥብ ያዝ/ዢ፡፡
- የፃፉትን የምት ሙዚቃ መሣሪያዎችን መቼ ፣የት እና በማን እንደተጫወቱ በቡድን ተወያይተዉ እንዲገልፁ በማድረግ ተጨማሪ ማብራሪያ ስጥ/ጪ፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ በቂ ጊዜ በመሥጠት አግዛቸዉ/ዢቸዉ፡፡

1. በአከባቢህ/ሽ የሚገኙ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች በመፃፍ አስረዳ/ጂ ፡፡
2. በአከባቢህ/ሽ የየሚገኙ ምት ሙዚቃ መሣሪያዎች በመሳል ለመምህርህ/ሽ አሳይ/ዪ፡፡
3. የፃፍከዉ/ሽዉ የየሚገኙ ምት ሙዚቃ መሣሪያዎች መቼ እና እንዴት እንደሚንጫወት አሳይ/ዪ፡፡

በመጨረሻ መልሱ እንደሚከተለዉ ማብራራት አለብህ/ሽ፡፡ የኦሮሞ ብሔረሰብ ብዙ የባሕላዊ ምት ሙዚቃ መሣሪያዎች አላቸዉ፡፡ በዚህ መሳሪያም ለተለያዩ ትዕይንቶች ይጠቀማሉ፡፡

**ለምሳሌ:**

- በበዓል ጊዜ
- የሠርግ ጊዜ
- በቤተ እምነት ተቋማት ዉስጥ የሚካሄዱ ትዕይንቶች፡፡
- መዝናናት በሚንፈልግበት ጊዜ
- ለተለያዩ ለባሕላዊ ጉዳዮች እና ወዘተ.....ናቸዉ፡፡

## የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች አይነት

ባሕላዊ እና ዘመናዊ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች በመባል ለሁለት ይከፈላሉ፡፡

## 1. ባሕላዊ እና ዘመናዊ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች

ከባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ታዋቂ የሆኑ ከበሮ፣መረካሻ፣መምቻ (ካባላ) እና ወዘተ...ናቸዉ፡፡

**ሀ.ከበሮ:-** ከቆዳ እና እንጨት ሊሰራ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሰዎች እንደተመቻቸዉ በተለያዩ ቅርጽ ይሰራሉ፡፡

ከበሮ በእጅ ወይም በሁለት መምቻ ዱላ እንጫወታለን፡፡

**ለ.መረከሽ፡-** መረከሽ ለተለያዩ ባሕላዊ ሥራዎች ይጠቀማሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሲወዛወዝ በሚያወጣ ድምፅ ለዘመናዊ ሙዚቃ ይጠቅማል፡፡ መረከሽ ቅል በማድረቅ እና ካሽ ካሽ የሚል ነገር ጨምረን በማወዛወዝ እንጫወታለን፡፡

**ሐ. መምቻ(ከበላ)፡-** ከባሕላዊ ሙዚቃ መሣሪያ አንዱ ሲሆን፣በሁለት እጅ ይዘን በመምታት እንጫወታለን፡፡ መምቻ ከጠፍጣፋ እንጨት ይሠራል፡፡

## 2.2 ቀላል የሆኑ ቅርፆችን ቀለም መቀባት

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: --7

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- ቀላል የሆኑ ቅርፅ ቀለም ይቀበሉ፡፡
- መሠረታዊ ቀለም በማደባለቅ፤የሚገኙ ቀለም ያስረዳሉ፡፡
- የቀጥተኛ ህትመት ዘዴ ይለያሉ፡፡
- የቀጥተኛ ህትመት አሠራር፤ ሠርተዉ ያሳያሉ፡፡
- የቀጥተኛ ህትመት ዝርዝር ይፅፋሉ፡፡

# መግቢያ

ቀላል የሆኑ ቅርጾችን ቀለም መቀባት ማለት፤የተፈጥሮ ሆነ ሠዉ ሰራሽ ነገሮች ያላቸዉን ቅርጽ በማየት ንድፍ ከነደፋችሁ በኋላ፣እንደየመልኩ በቀለም ማስዋብ ነዉ፡፡

የሚታይ ሥነ-ጥበብ (ቪዥዋል አርት) ችሎታ ለማበልፀግ ህይወት ያላቸዉና ህይወት የለላቸዉን ነገሮችን ደጋግመን የምንለማመድ ከሆነ፣ንድፍ ለመንደፍ እና ቀለም ቅብ እንዲችል ይረዳናል፡፡

# ቅድመ ዝግጅት

ይህን ርዕስ ለማስተማር የእለቱ ትምህርት ዓላማ ካዘጋጀህ/ሽ በኋላ የትምህርት ይዘቱን ለማስተማር የሚጠቅምህ/ሽ መርጃ መሣሪያ እርሳስ፣ወረቀት፣የተለያዩ ሥዕሎች ፣ብሩሽ እና የመሳሰሉትን አዘጋጅተዉ በክፍል መገኘት ጥሩ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- ገለፃ
- የጥንድ ዉይይት፣ቡድን እና በሙሉ ክፍል/ሁሉም ተማሪዎች አንድ ላይ፡፡
- በማየት
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

## ለ. የትምህርት መርጃ መሣሪያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣሪያዎች፡-

- የሚለማመዱበት ክፍል
- የተለያዩ ፎቶዎች
- ፖስተር
- ሞዴል
- እርሳስ፣የዉሃ ቀለም፣ ዉሃ ቀለም ብሩሽ እና በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

መምህር/ርት ቀላል የሆነ ቅርፅ ቀለም በመቀባት ምንነት እና ጥቅሙን ግለፅ፡፡ በመቀጠል በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ያለዉ ሂደት እና ቀድም ተከተል በመጠበቅ፤የቀላል ቅርፆች ቀለም አቀባብ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም አሳይ/ዪ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በመሕፃፍ ላይ የቀረበዉን ሥዕላ በማየት ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡ ከዚሃ በኋላ ሥዕሉን በመከተል በየግላቸዉ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡ በተጨማሪ እሂንን የመሰለ ስዕል ደብተራቸዉ በመሳል ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡
በመጨረሻ በዚህ ምዕራፍ የቀረቡትን ልምምድ በማሰራት ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

### ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ፅብረቃ
- የክፍል ልምምዶች
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ
- ፈተና

**ልምምድ 1. የቤት እና ጥጃ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀበቀ/ቢ፡፡**

**ተማሪዎች በመጽሐፍ ዉስጥ ልምምድ 1 የተጠቀሰዉ የቤት እና ጥጃ ንድፍ በወረቀት/ደብተር ላይ ከሳሉ በኋላ ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- ተማሪዎች የዚህ ልምምድ በመከተል የቤት እና ጥጃ ንድፍ ቀድመ ተከተሉን በመጠበቅ ደብተራቸዉ ላይ እንዲስሉ አድርግ/ጊ፡፡
- ይህን ንድፍ ከነደፉ በኋላ የእርስበርሳቸዉን በማየት ማን በትክክል ሠራ እያንዳንዳቸዉ እንዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡

- ተማሪዎች  እሄንን ንድፍ በደብተራቸዉ ላይ በትክክል መሣላቸዉን ተከታተል/ዪ፡፡
- በግል የሠሩትን ንድፍ፤በቡድን  እንዲወያዩ፣ እንዲተራረሙ  እና እንዲደናነቁ አድርግ/ጊ፡፡
- በመጨረሻ  ከተራረሙ  እና ንድፉ ትክክል መሆኑን ካረጋገጥክ/ሽ በኋላ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

**ልምምድ 2. የዶሮ እና የመሬት አቀማመጥ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀበቀ/ቢ፡፡**

**ተማሪዎች በመጽሐፍ ዉስጥ ልምምድ 2 የተጠቀሰዉ የዶሮ እና መሬት አቀማመጥ ንድፍ በወረቀት/ደብተር ላይ ከሳሉ በኋላ ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ።**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- ተማሪዎች የዚህ ልምምድ በመከተል የቤት እና ጥጃ ንድፍ ቀድመ ተከተሉን በመጠበቅ ደብተራቸዉ ላይ እንዲስሉ አድርግ/ጊ፡፡
- ይህን ንድፍ ከነደፉ በኋላ የእርስበርሳቸዉን በማየት ማን በትክክል እንደሠራ እያንዳንዳቸዉ እንዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች  እሄንን ንድፍ በደብተራቸዉ ላይ በትክክል መሣላቸዉን ተከታተል/ዪ፡፡
- በግል የሠሩትን ንድፍ፤በቡድን  እንዲወያዩ፣ እንዲተራረሙ  እና እንዲደናነቁ አድርግ/ጊ፡፡
- በመጨረሻ ከተራረሙ  እና ንድፉ ትክክል መሆኑን ካረጋገጥክ/ሽ በኋላ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

**ልምምድ 3. የወፍ ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀበቀ/ቢ፡፡**

**ተማሪዎች በመጽሐፍ ዉስጥ ልምምድ 3 የተጠቀሰዉ የወፍ ንድፍ በወረቀት/ደብተር ላይ ከሳሉ በኋላ ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ።**

- ይህን ንድፍ ከነደፉ በኋላ የእርስበርሳቸዉን በማየት ማን በትክክል እንደሠራ እያንዳንዳቸዉ እንዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች እሄንን ንድፍ በደብተራቸዉ ላይ በትክክል መሣላቸዉን ተከታተል/ዪ፡፡
- በግል የሠሩትን ንድፍ በቡድን እንዲወያዩ፣ እንዲተራረሙ እና እንዲደናነቁ አድርግ/ጊ፡፡
- በመጨረሻ ከተራረሙ እና ንድፉ ትክክል መሆኑን ካረጋገጥክ/ሽ በኋላ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

**ልምምድ 4. የአዉሮፕላን ንድፍ በመንደፍ ቀለም ቀባ/ቢ፡፡**

**ተማሪዎች በመጽሐፍ ዉስጥ ልምምድ 4 የተጠቀሰዉ የአዉሮፕላን ንድፍ በወረቀት/ደብተር ላይ ከሳሉ በኋላ ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ።**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- ተማሪዎች የዚህ ልምምድ ትዕዛዝ በመከተል የአዉሮፕላን ንድፍ ቀድመ ተከተሉን በመጠበቅ ደብተራቸዉ ላይ እንዲስሉ በመርዳት አበረታታቸዉ/ቺዉ፡፡
- የአዉሮፕላን ቀለም ምን አይነት እንደሆነ በመነጋገር፣ እያንዳዳቸዉ ተነስተዉ እንዲያስረዱ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች የአዉሮፕላን ቀለም በመለየታቸዉን በመከታተል አረጋግጥ/ጪ፡፡
- በመጨረሻ የአዉሮፕላን ንድፍ ነድፈዉ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

**ልምምድ 5. ከደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥእል በመሳል ቀለም ቀባ/ቢ፡፡**

**ተማሪዎች በመጽሐፍ ዉስጥ ልምምድ 5 የተጠቀሰዉ የአዉሮፕላን ንድፍ በወረቀት/ደብተር ላይ ከሳሉ በኋላ ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ።**

- ተማሪዎች የዚህ ልምምድ ትዕዛዝ በመከተል  የደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥእል ንድፍ ቀድመ ተከተሉን በመጠበቅ ደብተራቸዉ ላይ እንዲስሉ በመርዳት አበረታታቸዉ/ቺዉ፡፡
- የደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥእል  ንድፍ ቀለም ምን አይነት እንደሆነ በመነጋገር፤ እያንዳዳቸዉ ተነስተዉ እንዲያስረዱ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች የደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥዕል  ንድፍ ቀለም በመለየታቸዉን በመከታተል አረጋግጥ/ጪ፡፡
- በመጨረሻ  የደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥእል  ንድፍ ነድፈዉ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

## 2.3. የመሠረታዊ ቀለማት ድብልቅ እና ቀጥተኛ ህትመት

### 2.3.1 የመሠረታዊ ቀለማት ድብልቅ

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: --------------6

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

***ከዚህ ትምህርት ርዕሰ በኋላ ተማሪዎች፡-***

- *መሠረት ቀለም (የ1ኛ ደረጃ ቀለም ) ይፅፋሉ፡፡*
- *የመሠት ቀለም አደበላለቅ ሂዴት ይለያሉ፡፡*
- *የ2ኛ ደረጃ ቀለም ይፅፋሉ፡፡.*

**መግቢያ**

የቀለም ድብልቅ ማለት የተለያዩ አይነት ቀለማትን እኩል በሆነ ወይም ባልሆነ መጠን በማደባለቅ ነዉ፡፡

ለቀለም ቅብ የሚያገለግሉ ሦስቱ መሠረታዊ ቀለማትን በማደባለቅ የተለየ ቀለም መፍጠር ይቻላል፡፡

**ቅድመ ዝግጅት**

ይህን ርዕስ ለማስተማር የእለቱ ትምህርት ዓላማ ካዘጋጀህ/ሽ በኋላ የትምህርት ይዘቱን ለማስተማር የሚጠቅምህ/ሽ መርጃ መሣሪያ እርሳስ፣መሠረታዊ ቀለም፣ፓሌት (ቀለም ማደባለቂያ ሳሃን) ወረቀት፣ለህትመት የሚያገለግሉ ነገሮች ፣ብሩሽ እና የመሳሰሉትን አዘጋጅተዉ በክፍል መገኘት ጥሩ ነዉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- ገለፃ
- የጥንድ ዉይይት፣ቡድን እና በሙሉ ክፍል/ሁሉም ተማሪዎች አንድ ላይ፡፡
- በማየት
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

## ለ. የትምህርት መርጃ መሣሪያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-

- የሚለማመዱበት ክፍል
- የተለያዩ ፎቶዎች
- ፖስተር
- ሞዴል
- እርሳስ፣የዉሃ ቀለም፣ ዉሃ ቀለም ብሩሽ እና በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

በመቀጠል በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ያለዉ የፅሑፍ ሂዴት እና ቀድም ተከተል በመጠበቅ፤የቀለም አቀባብ ዘዴ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጠቀም አሳይ/ዪ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በመፅሐፍ ላይ የቀረበዉን ቀለም አደበላለቅ በማየት እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡ ከዚሃ በኋላ የተማሪዎች ላይ ያለዉን ንባብ በመከተል በየግላቸዉ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡ በተጨማሪ የቀለም አደበላለቅ በየቤታቸዉ ተለማምደዉ፤ ወደ ክፍል በማምጣት እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡

በመጨረሻ በዚህ ምዕራፍ የቀረቡትን መልመጃ እና ልምምድ በማሰራት ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ፅብረቃ
- የክፍል ልምምዶች
- የቤት ሥራ ፖርትፎሊዮ

- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ
- ፈተና

**የልምምድ 1 መልስ**

**በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ስለ ቀለም አደበላለቅ እንዲለዩ ማድረግ።**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- ✍ በመጀመሪያ ተማሪዎች የልምምድ ትዕዛዛ አንብበዉ እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡
- ✍ በመቀጠል ተማሪዎች የአንደኛ ደረጃ ቀለም በመቀባት፤ ሁለተኛ ደረጃ ቀለም ማግኘት እንደሚችሉ እና እንዲለዩ አድርግ/ጊ፡፡
- ✍ የተነገራቸዉን መረጃ/ነገር ከተረዱ በኋላ ትክክለኛ መልስ እንዲሞሉ መርዳት፡፡
- ✍ ትክክለኛ መልስ መመለሳቸዉን ለማረጋገጥ፤የርስበርሳቸዉን እንዲተራረሙ ምራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡ በመጨረሻም ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

**የልምምድ 1 መልስ**

1. ቀይ + ቢጫ = ብርቱካናማ
2. ቢጫ + ሠማያዊ = አረንጓዴ
3. ሠማያዊ + ቀይ = ወይነ ጠጅ

**መልመጃ 1**

**በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ስለ ቀለም አደበላለቅ እንዲለዩ ማድረግ።**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- በመጀመሪያ ተማሪዎች የልምምድ ትዕዛዛ አንብበዉ እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡
- በመቀጠል ተማሪዎች የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ቀለም አደበላለቅ እንዲለዩ አድርግ/ጊ፡፡
- የተነገራቸዉን መረጃ/ነገር ከተረዱ በኋላ ትክክለኛ መልስ እንዲሞሉ መርዳት፡፡
- ትክክለኛ መልስ መመለሳቸዉን ለማረጋገጥ፤የርስበርሳቸዉን እንዲተራረሙ ምራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡ በመጨረሻም ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

**የመልመጃ 1 መልስ**

1. ሦስት አሉ፡፡
2. ቢጫ፣ሠማያዊ
3. የሁለተኛ ደረጃ ቀለም እናገኛለን፡፡
4. ሦስት አሉ፡፡
5. ብርቱካን፣ ወይነ ጠጅ እና አሪንጓዴ ናቸዉ፡፡
6. 1. ሐ 2. ለ 3. ሀ

**መልመጃ 2. አዛምድ**

> **በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ስለ የቀለም መልክ እንዲለዩ ማድረግ፡፡**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- በመጀመሪያ ተማሪዎች የመልመጃ ትዕዛዛ አንብበዉ እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡
- በመቀጠል ተማሪዎች የቀለም መልክ እንዲለዩ አድርግ/ጊ፡፡
- የተነገራቸዉን መረጃ/ነገር ከተረዱ በኋላ ትክክለኛ መልስ እንዲሞሉ መርዳት፡፡
- ትክክለኛ መልስ መመለሳቸዉን ለማረጋገጥ፤የርስበርሳቸዉን እንዲተራረሙ ምራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡ በመጨረሻም ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

**የመልመጃ 2 መልስ**

**አዛምድ**

1. ሠ
2. መ
3. ሀ
4. ሐ
5. ረ
6. ለ

**መልመጃ 3 የአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ቻርት**

**በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ስለ አንደኛ እና ሁለተኛ ቀለማት ቻርት እንዲለዩ ማድረግ፡፡**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- በመጀመሪያ ተማሪዎች የመልመጃ ትዕዛዛ አንብበዉ እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡
- በመቀጠል ተማሪዎች የአንደኛ እና ሁለተኛ ቀለማት ቻርት ማወቃቸዉን ለይ/ዩ፡፡
- ከለዩ በኋላ የአንደኛ እና ሁለተኛ ቀለማት ቻርት፤ቀለም በማዘጋጀት በየቦታቸዉ እንዲቀቡ መርዳት፡፡
- በትክክለኛ ቦታ መቀባታቸዉን ለማረጋገጥ፤ የርስበርሳቸዉን እንዲተራረሙ ምራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡ በመጨረሻም መፅሐፍ ላይ በተቀመጠ መልክ መቀባታቸዉን ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

**ልምምድ 2. የቀስተ ደመና ንድፍ በመንደፍ ቀለም መቀባት**

**በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ፤ በተማሪዎች መፅሐፍ ልምምድ 2 ሥር ያለዉን ቀስተ ድምና ወተቀት ላይ ከሣሉ በኋላ ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ ማድረግ ነዉ፡፡**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- በመጀመሪያ ተማሪዎች የልምምድ ትዕዛዝ በመከተል የቀስተ ድምና ንድፍ ቀድመተከተሉን በመጠበቅ ለሥዕል በዘጋጁት ወረቀት ላይ እንዲሥሉ ማበረታታት፡፡
- የቀስተ ድምና ቀለማት እርስበርሳቸዉ በመነጋገር እያንዳንዳቸዉ ተነስተዉ እንዲነግሩ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች የቀስተ ድምና ቀለማት መለየታቸዉን አረጋግጥ/ጪ፡፡
- በመጨረሻም የቀስተ ደመና ንድፍ በመንደፍ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

### ልምምድ 3. ከደረት በላይ (ፖርትሬት) ንድፍ በመንደፍ ቀለም መቀባት

**በዚህ ልምምድ ተማሪዎች ፤ በተማሪዎች መፅሐፍ ልምምድ 3 ሥር ያለዉን ከደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥዕል ወተቀት ላይ ከሣሉ በኋላ ቀለም እየቀቡ እንዲለማመዱ ማድረግ ነዉ።**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- በመጀመሪያ ተማሪዎች የልምምድ ትዕዛዝ በመከተል የደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥዕል ንድፍ ቀድመ ተከተሉን በመጠበቅ ለሥዕል በዘጋጁት ወረቀት ላይ እንዲሥሉ ማበረታታት፡፡
- የደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥዕል ቀለማት እርስበርሳቸዉ በመነጋገር እያንዳንዳቸዉ ተነስተዉ እንዲነግሩ አድርግ/ጊ፡፡
- ተማሪዎች የደረት በላይ (ፖርትሬት) ሥዕል ያለዉን ቀለማት መለየታቸዉን አረጋግጥ/ጪ፡፡
- በመጨረሻም የደረት በላይ (ፖርትሬት) ንድፍ በመንደፍ ቀለም እንዲቀቡ አድርግ/ጊ፡፡

### 2.3.2 ቀጥተኛ ህትመት

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: ----5

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፀፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **የቅጠል ህትመት አሠራር ቅደም ተከተል ይገልፃሉ፡፡**
- **የቅጠል እና የመዳፍ ህትመት በክፍል ይለማምዳሉ፡፡**

## ሀ.የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- ገለፃ
- የጥንድ ዉይይት፣ቡድን እና በሙሉ ክፍል/ሁሉም ተማሪዎች አንድ ላይ፡፡
- በማየት
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

## ለ. የትምህርት መርጃ መሣርያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-

- የሚለማመዱበት ክፍል
- የተለያዩ ፎቶዎች
- ፖስተር
- ሞዴል
- እርሳስ፣የዉሃ ቀለም፣ ዉሃ ቀለም ብሩሽ እና በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች፡፡

### የመምህር/ርት ድርሻ

መምህር በመጀመርያ የቀጥተኛ ህትመት እና ጥቅሙን አስረዳ/ጂ፡፡ በመቀጠል በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ያለዉ ሥዕል ሂዴት እና ቀድም ተከተል በመጠበቅ፤ የቀጥተኛ ህትመት አሠራር በምሳሌ አሳይ/ዪ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች በመፅሐፍ ላይ የቀረበዉን ቀጥተኛ ህትመት በማየት እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡ ከዚሃ በኋላ የተማሪዎች ላይ ያለዉ

የቅጠል ህትመት፣ የእጅ መዳፍ እና ድንች የማተም ሥራ ቀድም ተከተል በመጠበቅ በየግላቸዉ እንዲለማመዱ አድርግ/ጊ፡፡

በተጨማሪ የቀለም ይህን የሚመሥል ሥዕል በደብተራቸዉ ላይ በቅጠል፣ መዳፍ እና ድንች በማተም በየቤታቸዉ ተለማምደዉ፤ ወደ ክፍል በማምጣት እንዲያትሙ አድርግ/ጊ፡፡ በመጨረሻ በዚህ ምዕራፍ የቀረቡትን መልመጃ እና ልምምድ በማሰራት ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

. **መልመጃ 1**

**በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ቀጥተኛ ህትመት በመለየት እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- ተማሪዎች የመልመጃዉን ትዕዛዝ በማንበብ፤ የቀጥተኛ ህትመት ቀድመተከተሉን በመጠበቅ በዘጋጁት ወረቀት ላይ በመስራት አስፈላጊ ነገር እንዲፅፉ መርዳት፡፡
- በመጨረሻም በየግላቸዉ የፃፉትን ነገር፤ በቡድን እንዲወያዩ፣ እንዲተራረሙ እና እነዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡

**የመልመጃ 1 መልስ**

1ኛ

- የዕፅዋት ቅጠል
- መዳመጫ
- ዝርግ የሆነ ነገር እና ጠረጴዛ
- ቀለም እና ብሩሽ
- የሚለጠፍበት ነገር ወረቀት፣ ክላሴር እና የመሳሰሉት ነገሮች፡፡
- ዉሃ እና ዉሃ የሚይዝ ዕቃ (ባልድ)

2ኛ

- ዝርግ የሆነ ነገር እና ጠረጴዛ
- ቀለም እና ብሩሽ
- የሚለጠፍበት ነገር ወረቀት፣ክላሴር እና የመሳሰሉት ነገሮችን ማዘጋጀት፡፡
- ዉሃ እና ዉሃ የሚይዝ ዕቃ (ባልድ)

**ልምምድ 1 በእጅ መዳፍ እና ቅጠል ህትመትን ማተም**

**በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ቀጥተኛ ህትመት በመለየት እንዲለማመዱ ማድረግ፡፡**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- ተማሪዎች የመልመጃዉን ትዕዛዝ በማንበብ፤ ስለ ቅጠል ህትመት፣ የእጅ መዳፍ እና ድንች ቀድመተከተሉን በመጠበቅ እንዲሰሩ መርዳት ፡፡
- በመጨረሻም በየግላቸዉ የፃፉትን ነገር፤በቡድን እንዲወያዩ፣ እንዲተራረሙ እና እነዲነጋገሩ አድርግ/ጊ ፡፡
- መምህር/ርት ከዚህ ምዕራፍ ያሉት ቀላል የሆኑ ቅርፅ ቀለም መቀባት፣የመሠረታዊ ቀለም አደበላለቅ እና ቀጥተኛ ህትመት ምን እንደተማሩ በመጠየቅ ግብረ መልስ ስጥ፡፡ ለምሳሌ ቀላል የሆኑ ቅርፅ ቀለም መቀባት፣ የመሠረታዊ ቀለም አደበላለቅ እና ቀጥተኛ ህትመትን በመለየት ቀለም መቀባታቸዉ እና ማተማቸዉን በማረጋገጥ፤ ከትምህርት ቤት መልስ ቤተሰቦቻቸዉ ስለ መሠረታዊ ቀለሞች እንዴት እንደሚያስረዳቸዉ እና የተለያዩ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያለዉን ሥዕሎችን እንደሚያሳዩ እና የመሳሰሉትን እንዲሰሩ አበረታቱ፡፡

# 2.4. የዲራማ ፣ቪድዮ እና ፎቶ መልዕክቶች

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: ----------7

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **በዲራማ፣ቪዲዮ እና ፎቶ መልዕክት ማስተላለፍ እንደሚቻል ይረዳሉ።**
- **በዲራማ፣ ቪዲዮ እና ፎቶ የሚተላለፈዉ መልዕክት ይለያሉ።**





## የዚህ ይዘት አንኳር ነጥብ:

- የዲራማ መልዕክት
- ዲራም በመፍጠር መለማመድ
- የቪዲዮ መልዕክት
- የፎቶ መልዕክት

## የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- የሚታደሙበት እና የሚለማመዱበት ክፍል
- የቪዲዮ መጫወቻ

## የመምህር/ርት ድርሻ

ቅድመ ንባብ ልምምድ አሠራ/ሪ፡፡ ማስተላለፍ በፈለጉት ነገር ላይ በመመሠረት አጭር ዲራማ በመፍጠር እንዲለማመዱ አግዛቸዉ/ዣቸዉ፡፡


መምህር/ርት በመጀመሪያ ዲራማ መልዕክት ማስተላለፍ እንደሚችል እና ምን አይነት መልዕክት እንደሚያስተላልፍ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የተሰጠዉን ሃሳብ በደንብ አስረዳ/ጂ፡፡ ለራሳቸዉም እንዲያነቡ አድርግ/ጊ፡፡

### ዲራማ መልዕክት

ዲራማ ወይም የትያትር ጫወታ የተለያዩ መልዕክቶችን ሰዉ ማዝናናት በሚችል እና በአጭር መንገድ ማስተላለፍ ይችላል፡፡ መልዕክት ከማስተላለፍ በዘለለ የተለያዩ ብሔረሰብ ባሕል እና ታሪክ ማስተማር እንደሚችል በምሳሌ አስረዱ፡፡

እንዲሁም የሰዉ ልጅ በዲራማ ሃዘኑን፣ደስታዉን፣ ፍቅርን አድናቆት እና የመሳሰሉትን መግለፅ ይችላል፡፡ በመድረክ ላይ ለተመልካች የሚቀርብ ዲራማ፣ ከላይ የጠቀስነዉን መልዕክት ማስተላለፍ ይችላል፡፡

በመቀጠልም የግንዛቤ ጥያቄዎችን እንዲሰሩ አግዝ/ዢ፡፡ ዲራማ አስተማሪ መሆን እንደሚችል ንገራቸዉ/ሪያቸዉ፡፡





**የግንዛቤ ጥያቄ-1**

**መልስ**

1. ታሪክ እና ባሕልን ያስተምራል፡፡

## የቪዲዮ መልዕክት

### የመምህር/ርት ድርሻ

- በቅድመ ንባብ ልምምድ የቀረበዉን የቪዲዮ ስዕል እንዲያዩ አድርግ/ጊ፡፡
- የቶሚና ጄሪ እና ፍሮዜን ሌሎች ቪዲዮችን አሳያቸዉ/ዩአቸዉ፡፡
- የቪዲዮ መልዕክትን መለየታቸዉን፤ ጥያቄ በመጠየቅ አረጋግጥ/ጪ፡፡
- በተለያዩ ቋንቋ ከተዘጋጁ የቪዲዮች የትኛዉን ማየት ትወዳላቸዉ ብለህ/ሽ ጠያቅ/ቂ፡፡
- ከዚሃ በኋላ ስለ ቪዲዮ እንደሚከተለዉ መሠረት ሥሬ ማብራሪያ አድርግ/ጊ፡፡







ቪዲዮ ማለት በፎቶ፣ድርጊት እና ድምፅ ቅንጅት ተቀድተዉ፤ በተሌ ቪዥን ወይም ሞባይል የሚታይ እና የሚሰማ ነዉ፡፡

ዲራማ ወይም ትያትር መልዕክት ማስተላለፍ እንደሚችል ሁሉ፤ ቪዲዮም የተለያዩ መልዕክቶችን ያስተላልፋል፡፡ በሌላ በኩል ለሕፃናት የተዘጋጀ ቪዲዮ ፊደል ፣ቁጥር፣ስለ ንፅህና ለማስተማር እንዲሁም በተለያዩ ጫወታወች ለማዝናናት በቴሌቪዥን የሚቀርብ ነዉ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄዎችን አሰራ/ሪ፡፡**

1. የእነኚን ሥዕሎች ቪዲዮ ማወቅ እና አለማወቃቸዉን ለይ/ዩ፡፡ ኤተዉ የሚያቁ ከሆነ፤ እነ ማን እንደሚባሉ አወያያቸዉ፡፡ ምን እንደተማሩባቸዉ በመጠየቅ አረጋግጥ/ጪ፡፡



2. ስለሚከተሉት የቪዲዮ ሥዕሎች ከጓደኞቻቸዉ ጋር እንዲነጋግሩ እርዷቸዉ፡፡

ከዚሃ በኋላ የሕፃናት ቪዲዮች ፊደል ፣ቁጥር፣ስለ ግል እና አከባቢ ንፅህና ለማስተማር እንዲሁም በተለያዩ መልክ ከተዘጋጁ በመምረጥ እንድያዩ/ ዕንዲታደሙ አድርግ/ጊ፡፡



## የፎቶ መልዕክት

**የመምህር/ርት ድርሻ**

*መምህር/ርት በምዕራፍ አንድ ስለ ፎቶ በሰፊ እንደተማሩ ንገራቸዉ/ሪያቸዉ፡፡ ፎቶ እንደ ዲራማ እና ቪዲዮ እራሱን የቻሌ መልዕክት የሚያስተላለፍ መሆኑን በሚከተለዉ መሠረት ሰፊ አብራራ/ሪ፡፡*



*የሚትተኛ ሕፃን ፎቶ*



*የሚትስቅ ሕፃን ፎቶ*

ሰዎች በተለያዩ ሁኔታ ዉስጥ ሆነዉ እና ድርጊቶችም እየፈፀሙ እያሉ ፎቶ ቢነሱ፣ ያፎቶ ሰዎቹ ያሉበትን ስሜት እና ምን እየሰሩ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ስለዚህ ፎቶ መልዕክት ማስተላለፍ ይችላል፡፡

## የግንዛቤ ጥያቄ 2

### መልስ

መጀመርያ ላይ ያለዉ ፎቶ እህል ሲወቃ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ሁለተኛ ፎቶ ደግሞ ፀጉር እየተሰራሩ ነዉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ፎቶ የሚንረዳ የእርስበርስ መረዳዳት እና የመተጋገዝ ባሕል ነዉ ብለዉ ከመለሱልህ/ሽ ተክክል ናቸዉ፡፡.




## የግንዛቤ ጥያቄ 3

### መልስ

ከሚከተሉት ዉስጥ መጀመርያ ላይ ያለዉ ፎቶ ከጓደኞቻቸዉ ጋር በደስታ የሚጫወቱ እና ፎቶ ለመነሳት የተሰበሰቡት ሲሆን ነዉ፤ሁለተኛ ፎቶ ደግሞ በራያ ህዝብ ባሕል ልብስ የተዋበች ህፃን የሚያሳይ ነዉ፡፡ መፅሐፋቸዉ ላይ ያለዉን የፎቶ መልዕክት እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡ በመቀጠል በግንዛቤ ጥያቄዎች ሥር ያሉትን የፎቶ መልዕክቶችን እንዲረዱ እና እንዲነግሩ አግዛቸዉ/ዣቸዉ፡፡





*ተከታታይ ምዘና*

- የግል እና ቡድን ዕብረቃ
- ግቡኝት
- ፖርትፎሊዮ
- ፈተና
- የቃል ጥያቄ

በመጨረሻም የተሰጠዉን መልመጃ አሰራ/ሪ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ጥያቄዎች አዘጋጅተህ/ሽ በቃል በመጠየቅ ወይም በማሰራት፤ የዚህን ምዕራፍ ዓላማ መረዳታቸዉን አረጋግጥ/ጪ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ 2**

- ➢ እህል/ገብስ የሚወቁ ቤተሰብ
- ➢ ፀጉር የሚሰራሩ እህታማሞች

**የግንዛቤ ጥያቄ 3**

- ➢ በራያ ባሕል ልብስ የተዋበች ህፃን የሚያሳይ ነዉ፡፡

**የመልመጃ 1 መልስ:**

1. አዝናኝ እና አጭር በሆነ መልክ፡፡

2. ፎቶ ስሜትን ብቻ ይገልፃል፣ቪዲዮ ግን በድርጊት፣ቃል እና ስሜትን ያንፀባርቃል፡፡

# ምዕራፍ 3 : የባሕል እና ታሪክ ተጨባጭ ሁኔታ

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: -----------20

## 3. የባሕል ዕሴት መግለጫ

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ የሚጠበቀዉ ዉጤት፡**

***ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-***

- የአከባቢያቸዉ ባሕል በሥነ-ጥበብ በማስተያየት ያሰላስላሉ፡፡
- በአከባቢያቸዉ የሚገኝ ታሪካዊ ቦታ እና ቤተ-መዘክር (ሙዚዬም) በመጎበኘት ያቀርባሉ፡፡
- የሃገራችን ሥነ-ጥበብ ሥራዎች በመሳል ያደንቃሉ፡፡

**ሀ. የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች**:

3.1. ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች--------(7 ክፍል ጊዜ)

3.2. ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሙዚቃ ሥራዎች--------(7 ክፍል ጊዜ)

3.3. ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ትያትር ሥራዎች----(6 ክፍል ጊዜ)

### ሀ.የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- የግል እና ጋራ ጫወታ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

### የትምህርት መርጃ መሣርያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-

- የተለያዩ ፎቶዎች
- የተለያዩ ትዕይንት የሚያሳይ ፎቶዎች፡፡
- ቪዲዮ እና የቪዲዮ መጫወቻ፡፡

- እርሳስ፣ክሮዉን፣ፓስትል፣ከሰል፣የዉሃ ቀለም፣ የዘይት ቀለም፣ ዉሃ ቀለም ብሩሽ እና በአከባቢ የሚገኙ የሥነ-ጥበብ መሣሪያዎች፡፡

*ተከታታይ ምዘና*

- የግል እና ቡድን ፅብረቃ
- ፈተና
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ
- የክፍል ልምምዶች
- የቤት ሥራ
- ፖርትፎሊዮ

## 3.1 ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ሥራዎች

### 3.1.1 የባሕላዊ ሥነ-ጥበብ ሥራዎች

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- ባሕላዊ እና ዘመናዊ የሥነ-ጥበብ ሥራ ይለያሉ፡፡
- ታሪካዊ ቅርስ ይፅፋሉ፡፡
- የሥፌት ሥራ ጥቅሞችን ይፅፋሉ፡፡.
- የሸክላ ሥራ ጥቅሞችን ይፅፋሉ፡፡.
- የቆዳ ሥራ ጥበብ ከምን እንደሚሠራ ይነግራሉ፡፡
- ከእንጨት የሚሠሩ ነገሮችን ይፅፋሉ፡፡
- ከብረታ ብረት የሚሠሩ ጌጣ ጌጦችን ይፅፋሉ፡፡

## ሀ.የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- ጥየቃ

## የትምህርት መርጃ መሣርያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-

- የተለያዩ ፎቶዎች
- የተለያዩ ትዕይንት የሚያሳይ ፎቶዎች፡፡
- ቪዲዮ እና የቪዲዮ መጫወቻ፡፡

## መምህር/ርት

የተጨባጭ ታሪክ እና ባሕል የሚል የትምህርት ርዕስ በሰሌዳ ላይ በመፃፍ ፅንስ ሃሳቡን ለተማሪዎች አስረዳ/ጂ፡፡ ተማሪዎች የታሪካዊ ቅርስ ቦታዎች፣በአከባቢያቸዉ የሚሰሩ የእጅ ሙያ ጥበብ ለምሳሌ፡-ሽመና፣የሥፌት ሥራ፣የብረታ ብረት ሥራ፣የእንጨት ሥራ፣የሸክላ ሥራ እና የቆዳ ሥራ እና ቤተ-መዘከር (ሙዚዬም) ፣ቤተ-መንግስት እን የመሳሰሉት ካሉ ሂዶ እንዲጎበኙ አመቻች/ቺ፡፡
የጎበኙትን ነገር ማለትም የታሪካዊ ቅርስ ቦታዎእና የእጅ ሙያ ጥበብ ከጥንት ጀምረዉ እስከ አሁን መሰራቱን አስረዳቸዉ/ጃአዉ፡፡
በደብተራቸዉ ላይ ማስታወሻ እንዲይዙ ንገራቸዉ/ሪዓቸዉ፡፡ የጎበኙትን ነገር ለክፍል ተወያይተዉ እንዲያቀርቡ ምራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡ ሲወያዩ ተከታተላቸዉ፣ በቡድን የተወያዩበትን ነገር ተራ በተራ እንዲያቀርቡ በማድረግ መልሱን በሰለዳ ላይ ጻፍ፡፡ ያቀረቡትን ሃሳብ ከተማሪዎች መፅሐፍ ጋር በማያያዝ ስለ እጅ ሙያ ጥበብ እና ታሪካዊ ቅርስ በሰፊዉ በመግለፅ አስረዳቸዉ/ጃቸዉ፡፡

ሥእል፣ፎቶ፣ሞዴል ወይም ዕዉነተኛ የሆኑ ቁሳቁሶች በእጅ ሥራ ጥበብ የተሠሩ እን የቤት እቃዎች ፣ባሕላዊ እና የመሳሰሉትንበማዘጋጀት ለተማሪዎች አሳይ/ዪ፡፡ የባሕላዊ እጅ ሥራ ጥበብ ለዘመናዊ እጅ ሥራ ጥበብ መሠረት እንደሆነ፤ በዚህ ቁሳቁሶች የተወሰነዉን አሳይ/ዪ፡፡ በዚህ ማሳያ ተማሪዎች እንዲሳተፉ በማበረታታት እንደ ደነቁ አድርግ/ጊ፡፡

## የመምህሩ ድርሻ

- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የተገለፀዉን የሥፌት ሥራ፣የሸክላ ሥራ፣የቆዳ ሥራ፣የሽመና ሥራ፣የእንጨት ሥራ እና ጠብረታ ብረት ሥራ ፎቶዎችን በማየት እንዲደነቁ አድርግ/ጊ፡፡
- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የተገለፀዉን በእጅ ሙያ ጥበብ የተሠሩ ቁሳቁሶችን ጥቅማቸዉን እንዲነግሩ አድርግ/ጊ፡፡
- በመጨረሻም በዚህ ምዕራፍ የቀረቡትን መልመጃዎችን በማሰራት ግብረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

### ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ፅብረቃ
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ

**መልመጃ 1**

**የዚህ መልመጃ ዓላማ ተማሪዎች ስለዚ ጥበብ የተወሰኑ እና አጠቃላይ መረጃ እንዲለዩ ማድረግ፡፡**

## የመምህር/ርት ድርሻ

- በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የለዉ ፎቶ በየግላቸዉ በማየት፤ በመልመጃ 1 የተሰጠዉን ጥያቄዎች እንዲመልሱ አድርግ/ጊ፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ሁሉም ጥያቄዎችን መሥራታቸዉን ተከታተል/ዪ፡፡ ችግር ባለበት ቦታ አግዛቸዉ/ዣቸዉ፡፡

✍ የዚህ ጥያቄዎች ዓላማ ተማሪዎች ባሕላዊ ጥበብ ለዘመናዊ ጥበብ ከቀረበዉ ፎቶ ምን ላይ እንደተረዱ መመዘን ነዉ፡፡

**የመልመጃ 1**

**መልስ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. ሀ | 2. ለ | 3. ሠ | 4. ሠ |
| 5. ሀ | 6. ሠ | 7. ሠ | 8. ሠ |

9. መልሱ እንደ ተማሪ አመላለስ ላይ የተመሠረተ ነዉ፡፡

### 3.1.2 ዘመናዊ የጥበብ ሥራ

**መልመጃ 1**

**የዚህ መልመጃ ዓላማ ተማሪዎች ስለ ቆዳ ጥበብ ሥራ የተወሰኑ እና አጠቃላይ መረጃ እንዲለዩ ማድረግ፡፡**

## ✍ የመምህር/ርት ድርሻ

✍ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የለዉ የክቡር ዶክተር አርትስት ለማ ጉያ ሥዕል በየግላቸዉ በማየት፣በመልመጃ 1 የተሰጠዉን ጥያቄዎች እንዲመልሱ አድርግ/ጊ፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ሁሉም ጥያቄዎችን መሥራታቸዉን ተከታተል/ዩ፡፡ ችግር ባለበት ቦታ አግዛቸዉ/ዣቸዉ፡፡

✍ የዚህ ጥያቄዎች ዓላማ ተማሪዎች ባሕላዊ ጥበብ ለዘመናዊ ጥበብ ከቀረበዉ ፎቶ ምን ላይ እንደተረዱ መመዘን ነዉ፡፡

**የመልመጃ 1**

**መልስ**

ቁርበት፣ስልቻ/ቀልቀሎ፣ከሪቻ፣ጫጬ፣ልጓም/ፉሎ፣መጫኛ እና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

## 3.2 የባሕላዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃ ታሪክ

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: ----------6

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **የሙዚቃን ታሪክ በአጭሩ ይገላፃሉ፡፡**
- **ሙዚቃ ለህብረተሰብ ያለዉ ጠቀሜታን ይፅፋሉ፡፡**

**አንኳር ነጥብ**

የባሕላዊ እና ዘመናዊ ሙዚቃ ታሪክ

### የመምህር/ርት ድርሻ

የቪዲዮ መጫወቻ እና ባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያ

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ገለፃ
- የቡድን ዉይይት

### ተከታታይ ምዘና

የተከታታይ ምዘና ሂዴት በመከተል፤በየቀኑ የሚያሳ ለዉጥ በማየት ግብረ መልስ በምስጠት፤የተሸለዉን ዉጤት መመዝገብ፡፡

### የመምህር/ርት ድርሻ

- ከአከባቢያቸዉ ሙዚቃ ታሪካ በመነሳት በአጭሩ አብራራ/ሪ፡፡
- ሙዚቃ ለህብረተሰቡ ያለዉን ጠቀሜታ፤ ተማሪዎችና ባሳተፈ መልክ አስተምር/ሪ፡፡
- ከዱሮ እስከ አሁን ያሉት ታዋቂ እና ተወዳጅ የኦሮሞ ድምፃዉን የቻሉትን ያህል በመዘርዘር እንዲገልፁ አድግ/ጊ፡፡በተጨማሪም በቂ ማብራሪያ እንደሚከተለዉ ስጥ/ጪ፡፡

ሙዚቃ ባሕል ከሚገለፅበት መሳሪያ አንዱ ነዉ፡፡ የሰዉ ልጅ ከተፈጠረነት ጊዜ ጀምረዉ የነበረ ነዉ፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ከጥንት ጊዜ ጀምረዉ በሙዚቃ ሲጠቀሙ ነበር፤ለምሳሌ በገዳ ሥርዓት የሚዘፈኑ ዘፈኖች እስከ ዛሬ ድረስ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የኦሮሞ ህዝብ ለተለያዩ ጉዳዮች በመጠቀም፤ባህሉን ከትዉልድ ወደ ትልውድ በማሸጋገር ነበር፡፡

የኦሮሞ ህዝብ ሙዚቃን ለተለያዩ ጉዳዮች ይጠቀማሉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- ሰርግ በሙዚቃ ያምራል፡፡
- በገዳ ሥርዓት በማዜም፤በመዝፈን
- ፖለቲካን በሙዚቃ
- ደስታ እና ሃዘን በሙዚቃ
- ሃገር የሚታዜሚበት መዝሙር አላት፡፡
- ጅግና በዘፈን ይታወቃል፡፡
- የሕፃናት ትምህርት በመዝሙር እንጂ አይሆንም፡፡
- በልማት ሥራ እርስበርሳቸዉን ለማበረታታት
- ኦሮሞ የተለያዩ መዝሙሮች አላት እና ወዘተ...ናቸዉ፡፡

ያለፈዉ ሥርዓት የኦሮሞ ብሔር ታሪክ እና ባሕል እንዳይታወቅ ከፍተኛ ጭቆና ያደረሰበት ቢሆንም፤የኦሮሞ ህዝብ ባደረጉት ትግል ለዉጥ ተገኝቷል ፡፡ በተለይ ድምፃዉያን እና ኣንጋፋ ፀሐፊዎች ባደረጉት ተሳትፎ ፤በሕብረተሰቡ ዘንድ ተወዳጅነት ያገኙ እና የማይረሱ ናቸዉ፡፡

ለምሳሌ፡-

- ✓ ዶክተር አሊ ብራ
- ✓ አቢተዉ ከበደ

- ✓ እልፍነሽ ቀኖ
- ✓ ሃሎ ዳዌ
- ✓ ኑሆ ጎበና
- ✓ ዘርሁን ወዳጆዉ
- ✓ ሂካ ዋጂ / ኦነስሞስ ናሲብ ከስድስት መቶ (600) በላይ መዝሙሮችን የፃፈ እና ወዘተ…ናቸዉ፡፡

የኦሮሞ ብሔረሰብ ሙዚቃን በዘመናዊ መልክ ለተለያዩ ጉዳይ እየተጠቀሙበት መሆናቸዉ ይታወቃል፡፡

**የሚከተሉትን ድርጊቶች ሰፊ ሰዓት በመስጠት፤ ተዘጋጅተዉ እንዲያቀርቡ አሳያቸዉ፡፡**

1. በአሁሉ ጊዜ በአከባቢያችሁ የኦሮሞ ህዝብ በሙዚቃ እየተጠቀሙ ናቸዉ?
2. አንደኛ መልስህ/ሽ "አዎን" ከሆነ ለም አይነት ጉዳይ እነደሆነ በመዘርዘር ለጓደኞችህ ግለጽ/ጪ፡፡
3. አሁን ያሉት ታዋቂ እና ተወዳጅ የኦሮሞ ድምፃዉን በመዘርዘር ሥራቸዉ እና ታሪካቸዉን የሚችሉት ያህል በመፃፍ ለክፍል ግለፁ፡፡

## 3.3. በትያትር የባሕል እሴቶች ከንዉን

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ --------7

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **የባሕል ዕሴት ምንነት ይረዳሉ፡፡**
- **"ጆቢዬ" የተሰኘዉ ባሕላዊ ጫወታ በትያትር በማሳየት ይገልፃሉ፡፡**

## የትምህርት መርጃ መሳሪያ

- የወሎ ባህል እና አልባሳት
- መለማመጃ ክፍል
- ጌጣ ጌጥ
- ከጫወታ ጋር የተያያዙ ሥዕል እና ፎቶዎች፡፡
- የቪዲዮ መጫወቻ/"ጀቢዬ" መዝሙር ለማስረዳት ዜማ

## የመምህር/ርት ድርሻ

**ቅድመ ንባብ ልምምድ አሰራ/ሪ፡፡**

ተማሪዎች በአከባቢያቸዉ የሚካሄድ እያንዳንዱ ባህል እና ዕሴት እንዲገልፁ በመጠየቅ ልምድ እንዲለዋዉጡ አድርግ/ጊ፡፡ መምህር/ርት በመጀመሪያ ስለ ባሕል ዕሴት መገለጫ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ የተፃፈ ሕፃናት እንዲያነቡ እዘዝ/ዢ፡፡ አንተም/አንቺም በበኩልህ/ሽ በደንብ እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡

የሚከተሉትን የባሕል ዕሴት ምሳሌዎች ይህ መሆኑን ንገራቸዉ/ሪያቸዉ፡፡

እሴት ህብረተሰቡ የሚተዳደርበት ህገ-መንግስት ነዉ፡፡


- ቋንቋ
- በዓል
- ክብረ በዓላት
- የዝከራ ቀን
- ባሕላዊ ምግብ
- የቤት አሰራር እን ቅርፃ ቅርፅ

ባሕላዊ የእሴት መገለጫ፤ እሴት የአንድ ህብረተሰብ አኗኗር ዘይቤ ዉስጥ የሚኖሪበት ደንብ በመሰየም እንደባህል አድርገዉ፤ ሲኖሪበት የነበረ እና አሁንም እየተጠቀመበት

ያለዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ባሕላዊ እሴት ከትዉልድ ወደ ትዉልድ የሚተላለፍ ሲሆን፤ የአንድን ብሄር ህዝብ ማንነት እና ቅርሶችን የሚያሳይ ነዉ፡፡ እነርሱም፡-

- ሙዚቃ
- ዉዝዋዜ
- ትያትር
- ሥነ ጥበብ
- ምልክቶች
- ክብረ በዓላት
- የእጅ ጥበብ ሙያ
- ትረካ እና ወዘተ…ናቸዉ፡፡

ስለዚህ የባሕል መገለጫ በትያትር ለማሳየት ሁሉንም ሥነ-ጥበባት በመጠቀም፤ የህብረተሰቡን እሴት ባህል ማሳየት ነዉ፡፡ ከዚሃ በኋላ የባህል እሴት ጠቀሜታ ንገራቸዉ/ንገሪያቸዉ፡፡



የባህል እሴት ጠቀሜታ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- የህብረተሰቡ ፈጠራ እንዲቆይ ያረጋል፡፡
- የባህል እሴት ቅርስ እንዲያድግ እና እንዲስፋፋ ያረጋል፡፡
- የሰዎችን አዕምሮ ይቀርፅል፡፡

በመቀጠልም የባህል እሴት ባህርያት ምን እንደሆነ ዘርዝርላቸዉ/ሊያቸዉ፡፡

## የህብረተሰብ እሴት ባህርያት

የባህል እሴት ባህርያት የሚከተለዉ ነዉ፡፡

- ከትዉልድ ወደ ትዉልድ ይተላለፋል፡፡
- ትረካ እና በድርጊት በማስመሰል
- የሕብረተሰቡን ባሕል እና ማንነት ይገልፃል፡፡
- የሕብረተሰቡን መስፋፋት ተከትለዉ ያድጋል፡፡

መምህር/ር ተማሪዎች የወሎ ኦሮሞ ባህል እሴት የጆቢዬ ተዉነት ፅሁፍ በመመስረት የተፃፈዉን በማንበብ ተረድተዉ እንዲጫወቱ እርዳቸዉ/ጃቸዉ፡፡

- ጆቢዬ  የወሎ ኦሮሞ ባህል እሴት ሲሆን ወጣቶች (ወንዶች እና ልጃገረዶች) የሚደናነቁበት ነዉ፡፡
- የጆቢዬ  ጫወታ በተለያየ ሁኔታ ይጫወታሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በሰርግ፣ ከብቶች ሲጠብቁ፣እንጨት ሲሰብሩ እና የመሳሰሉት ነወቸዉ፡፡
- ይህ ጫወታ ወጣቶች (ወንዶች እና ልጃገረዶች) አሪቲ እና ሎሚ ይዘዉ፣በባሕላዊ አልባሳት ተዉበዉ፣ ዋስንት መጫወት የሚችል ሰዉ ዋሽንት ይዘዉ እና የሚዘምሩበት ግጥም በማዘጋጀት፤ ፊትለፊት ተቀምጠዉ በዜማ እያዜሙ እና እየተወዛወዙ ይጫወታሉ፡፡

መምህር/ር ይህ ጫወታ ለተማሪዎች ግልፅ እንዲሆን፤ በመጀመሪያ የየወሎ ኦሮሞ ባህል እሴት ቪዲዮ ወይም ዘፈኖች ምሳሌ በመዉሰድ፤ በዜማ፣ተዉነት ፅሁፍ አእና ግጥም ከዋሽንት ጋር በመወዛወዝ በሚከተለዉ ሁኔታ እንዲጫወቱ አሳያቸዉ፡፡

*የጆቢዬ ዉዝዋዜ የሚያሳይ ሥዕል፡፡*

**የጆቢዬ ጫወታ ዘዴ**

ወንዶች በአንድ በኩል ሴቶችም በሌላ በኩል በመቀመጥ፤ዋሽንት ተጫዋቹን ተከትለዉ እንዲህ በማለት ጫዋታዉን ይጀምራሉ፡፡



**ወንዶች** **ተቀባይ**

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ: ወይቲ ላጋ ቡቱ ዛዊያ ጃላን

ህንድሌ ሰስት ሆፋ ናቤክ ማላን

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት :- ዋይቲ ሎላ ደምቱ ዝናራ ኬ ማርፋዱ

የሮ ናማ ብራ ናት ሙሙፋዱ

ዋይቲ ቆፋ ቆፋ ማሪ ናዱንጋዱ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ወንድ:- ካንጅቤ ሃ ጅቡ ሃቦኮኩ ማሌ

አን ፋጤ ህንዲሱ ኤርጋ ራቢ ማሌ

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት:-ጎጆ ዱባ ጋላ እት ጋላን ማና

ዋል ብራ ኑ አርጌ ማልቱ ኑ አማና

ጆቢዬ　　　　　　　　　　　　　አጆባ ጆብ

ወንድ: ዋሊን ኦሉ ኬኛ ናምን ኑ ሀማታ

ጃላል ሃማዳ ዮም ካና ሶዳታ

ጆቢዬ　　　　　　　　　　　　　አጆባ ጆብ

ሴት:　ጫፋ ዲዳ ጋርቢ

ኬሱማ ፋካዱ ሁላ ኬኛን ዳርብ

ጆቢዬ　　　　　　　　　　　　　አጆባ ጆብ

ውንድ: ጫፋ ላጋ ጋዲ እልሞ ሳላ ዲዳ

ማና ኬሳን ሴሂ አሴነ ማስጂዳ

ጆቢዬ　　　　　　　　　　　　　አጆባ ጆብ

ሴት:　አኖ ሲን ጃላዳ ሲ ጂቤቲ ምቲ

ሃማ አማ ቱሩን ኮ አዮ ሶዳዴት

ጆቢዬ　　　　　　　　　　　　　አጆባ ጆብ

ወንድ:ኤርጋ አካስ ጀቴን ሻጌ ዱቢን ቶለ

አስ ኮቱ ናቃብ አን ኦፍ ዋላሌ

ጆቢዬ　　　　　　　　　　　　　አጆባ ጆብ

ሴት:　ቢሻኒን　ዋራባ ኦኮሌ ላማን

ዋል ፉዳኔ ባና ኅርዶማ ጃላን

ጆቢዬ　　　　　　　　　　　　　አጆባ ጆብ

ወንድ፡ ጎጆ ግዱ ጋላ ቃሩራን ካባኒ

ስን ልቅምሳን ቱሬ ሲማሌ ህንቃባን

**ጆቢዬ** **አጆባ ጆብ**

ሴት፡ ጎጆ ግዱ ጋላ ቃሩራን ካባኒ

አት ናልቅምስ እሳን ዋል ዳባን

መምህር/ርት ተማሪዎች ይህን የመሰለ በአከባቢያቸዉ የሚታወቀዉ የባሕል ዕሴት ካሌ ለክፍል እንዲያቀርቡ እድርግ/ጊ፡፡ የማያቁት ከሆነ ቤተሰባቸዉን ጠይቀዉ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

- የቡድን ማሳያ/ ትዕይንት
- የግል እና ቡድን ገለፃ
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ

በመጨረሻም መልመጃዎችን አሰራ/ሪ፡፡

**የመልመጃ 1 መልስ**

1. የህብረተሰቡን ፈጠራ እንዳሌ ይጠብቃል፣ ይህ የባህል ዕሴት እንዲስፋፋ እና እንዲያድግ ያደርጋል፣ የሰዎችን አዕምሮ ይቀርፃል፡፡

2. ሠ
3. መ

**የመልመጃ 2 መልስ**

1. የተዋደዱ ሰዎች ለእርስበርሳቸዉ መሥዕዋትነት እንዲከፍሉ ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ 4 : የሥነ ጥበባት መሥዕብ

## 4 የሥነ ጥበባት ሥራዎች አድናቆት

### 4.1 የስነ ጥበብ አድናቆት

*ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: -----------25*

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ የሚጠበቀዉ ዉጤት፡**

***ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-***

- **የሃገራችን ሥነ ጥበባት ሥራዎችን በመዝሙር፣ሥዕል፣ በዉዝዋዜ እና ገፀ- ባሕሪ በመጫወት ያደንቃሉ።**

***ሀ.የምዕራፉ አንኳር ይዘቶች***

*ሀ. የሥነ-ጥበብ አድናቆት*

*ለ. የሙዚቃ አድናቆት እና*

*ሐ. የሥነ- ትያትር አድናቆት*

### ለ. የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- የግል እና የቡድን ጫወታ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

### ሐ.የትምህርት መርጃ መሣርያ

*የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-*

- የተለያዩ ፎቶዎች
- የተለያዩ ትዕይንት የሚያሳይ ፎቶዎች፡፡
- ቪዲዮ እና የቪዲዮ መጫወቻ፡፡

## መ. ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ዕብረቃ
- የክፍል ልምምድ
- የቤት ሥራ
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ
- ፈተና

### 4.1 የሥነ-ጥበብ አድናቆት

ለዚህ ትምህርት የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: --------9

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **የሥነ-ጥበብ ሥራ ያደንቃሉ፡፡**
- **የሃገራችን የእጅ ሙያ ጥበብ ከምን እየተሰራ እንደነበር ይዘረዝራሉ፡፡**

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- የግል እና የቡድን ጫወታ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

## ሐ.የትምህርት መርጃ መሣርያ

የትምህርቱን ይዘት ለማስተማር የሚያስፈልጉ መርጃ መሣርያዎች፡-

- የተለያዩ ፎቶዎች
- የተለያዩ ትዕይንት የሚያሳይ ፎቶዎች፡፡
- ቪዲዮ እና የቪዲዮ መጫወቻ፡፡

### መምህር/ርት

የትምህርቱን ርዕስ "የሥነ-ጥበብ አድናቆት"
የሚለዉን በሳሌዳ ላይ በመፃፍ ፅንስ ሃሳቡን ለተማሪዎች ግለፅ/ጪ፡፡ ተማሪዎች የሃገራችን ጥበብ ሥራዎች፣ በአከባቢያቸዉ የሚሠሩ እና የሚገኙ ስራዎች ከምን እየተሰራ እንደነበር አስረዳቸዉ/ጃቸዉ፡፡ የነገርካቸዉ/ሻቸዉን ነገር በአከባቢያቸዉ ከሚገኝ ነገሮች መስራት እንደሚቻል አስረዳ/ጂ፡፡ ደብተራቸዉ ላይ እንዲፅፉ ንገራቸዉ፡፡ በአከባቢያቸዉ ከሚገኝ ነገሮች ሥዕል ሥለዉ ለክፍል እቅርበዉ እንዲወያዩበት በመከታተል ምራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡

ተማሪዎች በቡድን የተወያዩበትን ሃሳብ በየተራ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ በሳሌዳ ላይ ፃፍ/ፊ፡፡ የሰጡትን ሃሳብ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ከተገለፀዉ ጋር በማያያዝ ስለ ሃገራችን ባሕላዊ ሥነ-ጥበብ በሠፊዉ አስረዳ/ጂ፡፡
ሥዕል፣ፎቶ፣ሞዴል ወይም በአከባቢያቸዉ ከሚገኙ ነገሮች የእጅ ሙያ ጥበብ የሚሰሩ፡- የቤት ቁሳቁስ፣ባሕላዊ መሳሪያዎች እና የመሳሰሉትን በማዘጋጀት ለተማሪዎቸች አሳይ/ዪ፡፡ የጥንት ዘመን የእጅ ሙያ ለዘመናዊ የእጅ ሙያ መሠረት እንደሆነ ለተማሪዎቸች አስረዳ/ጂ፡፡ በዚህ ማሳያ ተማሪዎች በመሳተፍ፣ እንዲደነቁ አድርግ/ጊ፡፡

### የመምህር/ርት ድርሻ

መምህር/ርት በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ያለዉ የእጅ በእጅ ሙያ ሥራዎችን የሚያሳዩ ሥዕሎችን በማሳየት፣ ስለ ሥዕሉ እና ከምን እንደተሰሩ በመገመት እንዲነግሩ አድርግ/ጊ፡፡ በመቀጠል የሃገራችን ባሕላዊ ሥነ-ጥበብ ማለት ምን እንደሆነ ከነገርክቸዉ/ሻቸዉ በኋላ፣ እያንዳናዳቸዉን በማስተያየት ንገራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡

በመጨረሻም ተማሪዎች የሥነ-ጥበብ አድናቆት ስሜት እንዲኖራቸዉ፣ እንዲያሳድጉ፣ ለይተዉ ማወቃቸዉን እና መረዳታቸዉንበመከታተል ግበረ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

በጥንት ዘመን በአከባቢ ከሚገኙ ነገሮችን የተሠሩ የጥበብ ሥራዎች አሉ፡፡ለምሳሌ፡- ከጅማት ክራር እየሰሩ፣ከሸንቦቆ ዋሽንት፣ከቀጭኔ ቆዳ ከበሮ፣ከቅል ወተት ማጠራቀሚያ ፣ከቃጫ ጅባ፣ከጥጥ ልብስ፣ከሥንደዶ ስፌትን፣ከዘንባባ ሳሌን ና የመሳሰሉትን መሥራት እንደሚቻል፤ ተማሪዎች መረዳታቸዉን ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና በመከታተላ ያለዉን ስህተት አስተካክል/ዪ፡፡

## ሀ.ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ጽብረቃ
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄዎች

## 4.2 የባሕላዊ ሙዚቃ አድናቆት

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: --9

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **የአከባቢያቸዉን ባሕላዊ ሙዚቃዎች ዘርዝረዉ፤ በደረጃ በማስቀመጥ ያደንቃሉ፡፡**

**አንኳር ነጥብ**

- የባሕላዊ ሙዚቃ አድናቆት

## የትምህርት መርጃ መሣሪያ

መለማመጃ ክፍል፣ የሙዚቃ ድምፅ መጫወቻ፣ የምት ሙዚቃ መሣሪያዎች

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- የግል እና የቡድን ዕብረቃ
- ገለፃ
- ፖርትፎሊዮ እና የመሳሰሉት

## ተከታታይ ምዘና

የተከታታይ ማዘና ሂዴት መከታተል እና በየቀኑ የሚያሳዩትን ለዉጥ በማየት ግብረ መልስ መሥጠት እና የተሸለ ዉጤት መያዝ፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

- የአከባቢያቸዉን ባሕላዊ ሙዚቃዎች ዘርዝረዉ፤ በደረጃ በማስቀመጥ እንዲያደንቁ፤ በማነቃቃት የተሰጣቸዉን ድርጊት እንዲሰሩ አሳያቸዉ፡፡

**የሚከተሉትን ድርጊት እንዲሰሩ አድርግ/ጊ፡፡**

1. የአከባቢያቸዉ ባሕላዊ ሙዚቃ እንዲዘረዝሩ አድርግ/ጊ፡፡
2. ከአከባቢያቸዉ ባሕላዊ ሙዚቃ ዉስጥ ታዋቂ የሆኑ በመለማመድ፤ ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡
3. ከቀረቡት የባሕላዊ ሙዚቃ የቱን በይበልጥ እንደሚወዱ እና እንደሚያደንቅ በደረጃ በማስቀመጥ እንዲገልፁ አድርግ/ጊ፡፡

## 4.3 ጫወታን በትያትር

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: --8

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

*ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-*

- **በባሕላዊ ሥነ-ጥበብ በመጠቀም ጀግኖቻቸዉን ያደንቃሉ።**

## የይዘቱ አቢይ ነጥብ

- የህብረተሰቡን ሥነ-ጥበብ ያደንቃሉ፡፡
- ጌራርሳ (ቀረርቶ)
- በጌራርሳ (ቀረርቶ) ጀግኖችን ያደንቃሉ፡፡

## የትምህርት መርጃ መሣሪያ

- የመለማመጃ ክፍል
- የወሎኦሮሞ ባህላዊ ልብስ
- ሚዶ/ ማበጠሪያ
- እርሳስ
- ወረቀት

በባለፈዉ ትምህርት እና በተለያየ ምዕራፍ ዉስጥ የተማሩትን መሠረት በማድረግ የኦሮሞ ህዝብ አኗኗር በጥበብ የተሞላ መሆኑን የህብረተሰቡን እሴት ምሳሌ በመዉሰድ አስረዳ/ጂ፡፡

## የመምህር/ርት ድርሻ

- የልምምድ ጥያቄዎችን አሰራ/ሪ፡፡
- ስለ ጌራርሳ (ቀረርቶ) ሰምተዉ የሚያዉቁት ነገር ካለ ለክፍል እንድያስረዱ ጠይቃቸዉ፡፡

- የሚያርራራ ሰዉ አይተዉ የሚያዉቁ ከሆነ፤ ምን አይነት ድርጊት እንደሚያሳዩ በስሜታዊ እንቅስቃሴ እንዲያሳዩ አድርግ/ጊ፡፡
- የሚያርራራ ሰዉ ምን እንደሚይዝ እንዲነግሩ እርዳቸዉ/ጃቸዉ፡፡
- ቀረርቶን በድርጊት ደስ ካሰኛቸዉ ይግለፁ፡፡

መምህር/ርትአንተም/አንቺም የተለያዩ ትዕይንቶች በጥበባዊ መልክ መግለፅ እንደሚቻል ለተማሪዎች በደንብ ግለጽ/ጪ፡፡ ይህም የኦሮሞ ህዝብ ጀግናዉን ሲያሞግስ፣ ፈሪን ሲያጥላላ፣ ዳር ድንበሩን ሲጠብቅ፣ ከብቶቹን ሲጠብቅ፣ሲያጋባ በጥበባዊ መልክ መልዕክቱን እንደሚያስተላልፍ ንገራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡ የኦሮሞ በጥበባዊ ትዕይንት ጀግናን ማወደስ አንዱ መሆኑን በማስረዳት ኦሮሞ በቀረርቶ አእንዲጠቀሙ፤ የተማሪዎች መፅሐፍ ላይ በተፃፈ መሠረት ከተገነዘብከዉ/ሽዉ ነገር በሠፊዉ ግለጽ/ጪ፡፡ ሲያቅራሩ ሁለት ሰዉ ወይም በቡድን በመሆን፤ ባሕላዊ መሣሪያዎች እንደነ ጋሻ እና ጦር በመያዝ የተለያዩ እንቅስቃሰዎችን በማሳት፣ እየተቀባበሉ እንደሚያቅራሩ አስረዳቸዉ/ጃቸዉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በህብረተሰባቸዉ ጌራርሳ (ቀረርቶ) በመጠቀም የወሎ ጀግኖችን እንዲያወድሱ አግዛቸዉ/ዣቸዉ፡፡

ስለ ጌራርሳ ጫወታ በተማሪዎች መፅሐፍ ላይ ባለዉ መሠረት ለተማሪዎች አናብብ/ቢ፡፡ ይህ ጫወታ የግጥም እና ዜማ ቅንጅት የሚታይ ነዉ፡፡ ስለዚህ መልዕክቱን በደንብ አስረዳ/ጂ፡፡ከዚሃ በኋላ ተማሪዎች ገፀ ባህርይ በመከፋፈል እሄንን ግጥም እንዲሸምድዱ በመርዳት፤ በመድረክ ላይ እንዲያቀርቡ አድርግ/ጊ፡፡

## በጌራርሳ (ቀረርቶ) ጀግኖች ማወደስ



ተማሪዎች የወሎ ባሕላዊ ልብስ ለብሰዉ፣ሚዶዉን ሰክተዉ፣መፋቅያ ይዘዉ፣ዝናር በሚመስል ነገር ወገባቸዉን ታጥቀዉ፣ዱላ ይዘዉ ይጫወታል፡፡



በመጀመርያ አንድ ተማሪ ብቻዉን ተቀምመዉ በሃሳብ እያጉረመረመ ፤ ከጓደኞቹ ፊትለፊት ሁለት ለሁለት ይገባሉ፡፡

**1ኛ ሴት ተማሪ: ማል ታቴ ያዶፍታ?**

**1ኛ ወንድ ተማሪ : ጎቶታ ኬኛ ያዴ**

**2ኛ ሴት ተማሪ: ዋሎ ጀቱን ዋሎ**

**ኑህ ሲፍ ጅራ ህን ያዳእን ማሎ**

**ተማሪዎች በቡድን: ሃ…ሃ….**

**1ኛ ወንድ ተማሪ : ናን ያዳዴ ማሌ ታካ ህን ያዶፍኔ**

ዋሎ ታኡ ኬኛ አን ህን እራንፋኔ

ያዶ እሼ ህን ቃብኑ ጃግና እራ ዳላኔ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

1ኛ ወንድ ተማሪ፡ እልማን ሃሳን አሜ

ዳዌ እራ ራቅሜ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

2ኛ ወንድ ተማሪ: እጆሌን ዋዳይ፣ዋዳይ ባቦ ጃራ

ጂሌራ ማንዲሂ ዲና አሪኤ ኦፍ እራ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

3 ኛ ወንድ ተማሪ : ካን ኡስማን ጥዬ ፌ ካን ኡማር ቡሹራ

ሳባር ሳካ ጆቻ ፉላሃን ዋዩራ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

1ኛ ወንድ ተማሪ : ካን እማም ዩሱፍ

ጋርፋራን ዱፉፍ

ዲና ሆንጌሱፍ

ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....

1ኛ ሴት ተማሪ : አንስ ካን ዋርቅቱ

**ዱካና ኬ እፍቱ**

**ጢቂን ናት ህን ሃፍቱ**

**ተማሪዎች በቡድን: ሃ...ሃ....**

**1ኛ ወንድ ተማሪ : ኮርም ጋፋ ሎሌ**

**ሁሉም ተማሪዎች: ሃ..ሃ...ሃይ ኮርማን ጋፎ**

**1ኛ ወንድ ተማሪ: እንጂፋኖን ጋሌ**

**ሁሉም ተማሪዎች:ሃ..ሃ...ሃይ ኮርማን ጋፎ**

በማለት ከመድረክ ይወርዳሉ

በመጨረሻም በአካባቢያቸዉ ከዚህ ጋር የተያያዘዉን ባሕል የሚያዉቁ ከሆነ፣ ለእርስበርሳቸዉ ይነጋገሩ ወይም ቤተሰባቸዉን ጠይቀዉ በመምጣት እንዲሁም የሚወዱትን ጀግና ገፀ-ባሕርይዉን እንዲያደንቁ አድርግ/ጊ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

- የቡድን ጽብረቃ
- የግል እና የቡድን ገለፃ
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ

መልመጃዉን በማሰራት ግንዛቤያቸዉን አረጋግጥ/ጪ፡፡

**የመልመጃ መልስ**

1. ሃሳን ኣሜ፣ዋዳይ ባቦ ጃራ፣ኡስማን ጥዬ፣ኡማር ቡሹራ፣ኢማም፣ ዩሱፍ እና ጀግኒት ወርቅቱ ናቸዉ፡፡
2. ዳዌ፣ጂሌ፣ዋ እና ጋርፋ

# ምዕራፍ 5 : የሥነ-ጥበባት ትስስር

## 5.1 ሥነ-ጥበባት መካከል ያለዉ ግኑኝነት

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ አጠቃላይ ክፍለ ጊዜ --20**

### የምዕራፉ አንኳር ይዘቶች

- ሥነ-ጥበባት መካከል ያለዉ ግኑኝነት
- ሥነ-ጥበባት ሌላ ትምህርት በማስተማር ዉስጥ ያለዉ አስፈላጊነት

### ሀ.ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- የግል እና የቡድን ጫወታ
- ገለፃ
- ጥያቄ እና መልስ
- በተግባር ማሳየት

### ለ.የትምህርት መርጃ መሣርያ

- የተለያዩ ፎቶዎች
- የተለያዩ ትዕይንት የሚያሳይ ፎቶዎች፡፡
- ቪዲዮ እና የቪዲዮ መጫወቻ፡፡

### ሐ. ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ዕብረቃ
- የክፍል ልምምድ
- የቤት ሥራ
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ
- ፈተና

## የመምህር/ርት ድርሻ

- በመጀመርያ በተማሪ መፅሐፍ ላይ ያለዉን ቀለማትን ለተማሪዎች አሳይ፡፡ የቀለማትን መልክ አብራራ/ሪ፡፡
- በመቀጠልም ሥነ-ጥበብ መማር ዉስጥ ያለዉ የሙዚቃ ትምህርት አስፈላጊነት በመለየት ለተማሪዎች ግለፅ/ጪ፡፡
- . ሙዚቃን በመጠቀም ቀለማትን እንዴት ማስተማር እንዳለብን ካስረዳህ/ሽ በኋላ፤ የቀለማትን መልክ ከአከባቢያቸዉ ጋር በማያያዝ መረዳታቸዉን እና እንደየመልካቸዉ በመለየት ጠይቃቸዉ፡፡ መጀመሪያ በግላቸዉ እንዲመልሱ አድርግ/ጊ፡፡ ከዚሃ በኋላ ለእርስበርሳቸዉ እንዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡ እነሱ ሲነጋገሩ አድምጣቸዉ/ጫቸዉ፡፡ በመጨረሻም የተስተዋልከዉን/ሽዉን ስህተት በመለየት አስተካክል/ዪ፡፡
- ከዚሃ በኋላ መልመጃዎችን በየግላቸዉ እንዲሰሩ  አድርግ/ጊ፡፡ እርስበርሳቸዉን የሳሉትን ሥዕሎች እንዲይዩ አድርግ/ጊ፡፡ አንተም/ቺም በማየት እና በመከታተል ስህተት እየለየህ/ሽ  እያስተካከል/ዪ፡፡
- በመጨረሻም ሌሎች ትምህርት በማስተማር ዉስጥ ያለዉ የሥነ-ጥበብ አስፈላጊነት የሚያዉቁትን ነገር ይነጋገሩ፤ የማያዉቁትን  ደግሞ ቤተሰቦቻቸዉን ጠይቀዉ በክፍል እንዲነጋገሩ አድርግ/ጊ፡፡ ሌሎች በመማር ዉስጥ ካለዉ የሥነ-ጥበብ አስፈላጊነት የተማሩትን ነገር በመለየት ፤ ተማሪዎችን ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተስተዋልከዉን/ሽዉን ስህተት በመለየት አስተካክል/ዪ፡፡

## ተከታታይ ምዘና

- የግል እና ቡድን ፅብረቃ
- የክፍል ልምምድ
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቄ
- የሙከራ ጥያቄ

## 5.2 የሥነ-ጥበባትሌሎች ትምህርት መማር ዉስጥ ያለዉ አስፈላጊነት

### 5.2.1 ሌሎች ትምህርት መማር ዉስጥ ያለዉ የሙዚቃ አስፈላጊነት.

#### ሀ.ማስተማር ዘዴዎች

- ግቡኝት
- ገለፃ
- የጥንድ፣ቡድን እና ሙሉ ክፍል ዉይይት
- ጥያቄ እና መልስ
- የግል እና ጋራ ገለፃ
- በተግባር

#### ለ.የትምህርት መርጃ መሣርያ

- የሚለማመዱበት ክፍል
- የተለያዩ ፎቶዎች
- ፖስተር
- ሞዴል
- እርሳስ፣ክራዎን እና ፔስትል፣ከሰል፣የዉሃ ቀለም፣የዘይት ቀለም እና በአከባቢያቸዉ የሚገኝ የሥነ-ጥበብ መሣሪያዎች፡፡
- የሙዚቃ ድምፅ መጫቀቻ
- የምት ሙዚቃ መሣሪያ

#### ተከታታይ ምዘና

የተከታታይ ምዘና በመከተል፤ የሚያሳዩትን ለዉጥ በማየት እና ግብረ መልስ በመስጠት የተሸለዉን ዉጤት ያዝ/ዢ፡፡

**መምህር/ርት ድርሻ**

- በመዝሙር በመጠቀም የትኛዉን ትምህርት እንደተምሩ፤ ልምዳቸዉን እንዲዘረዝሩ አድርግ/ጊ፡፡

- ሕፃናት ማስተማሪያ ወይም ትምህርት የተቀዳበት ክሊፕ ሞባይል በመጠቀም ከእንተርኔት በማዉረድ፤ እንዲታደሙ/እንዲያዩ አድርግ/ጊ፡፡ ለምሳሌ፡- "*ተረት..ተረት..ቀለም ምንድነዉ*" የሚል በመገርሳ በቀለ የተዘጋጀዉን መዝሙር ከእንተርኔት ማዉረድ ይቻላል፡፡
- በመጨረሻም መዝሙር ሌሎች ትምህርት በማስተማር ሂዴት ዉስጥ ያለዉ ጠቀሜታ እና ግኑኝነት ግለፅ፡፡

## 5.2.2 *ሥነ-ትያትር እና ሌሎች ትምህርት ግኑኝነት*

ለዚህ ትምህርት ርእስ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ: --10

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናፅፉ የሚገበ የመማር ብቃት፡**

***ከዚህ ትምህርት ርዕስ በኋላ ተማሪዎች፡-***

- *ሥነ-ትያትር ሌሎች ትምህርት መማር ዉስጥ ያለዉ ጠቀሜታ ይረዳሉ፡፡*
- *የሥሜት ሕዋሳትና በትያትር ይገልፃሉ፡፡*

**የዚህ ይዘት አንኳር ነጥብ**

- *የሥነ-ጥበባት ግኑኝነት*
- *ሥነ-ትያትር ሌሎች ትምህርት መማር ዉስጥ ያለዉ ድርሻ*

*የሥሜት ሕዋሳት*

### *የመርጃ መሣሪያዎች*

- *የልምምድ ክፍል*
- *የሥሜት ሕዋሳት ፎቶ/ሥዕል*

## *የመምህር/ርት ድርሻ*


በተፈጥሮ ሳይንስ ስለ ሥሜት ሕዋሳት መምህር የነገራቸዉን ገፀ ባሕርይ በመጫወት ማሳየት እንደሚቻል ንገራቸዉ/ሪዐቸዉ፡፡ ተማሪዎች ስለ ሥሜት ሕዋሳት ገፀ ባሕርይ በመጫወት በደንብ እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡


በመፅሐፋቸዉ ላይ ያለዉ የሥሜት ሕዋሳት ያደረጉት ቃለ-ምልልስ በመከታተል እንዲረዱ አድርግ/ጊ፡፡


**የሥሜት ሕዋሳት ጫወታ**



አንድ ቀን እነዚህ አካላት ተጣልተዉ፤በጣም ተከራከሩ፡፡ ሁላቸዉም እንደሚከተለዉ ተራ በተራ በማካበድ እራሳቸዉን ገለፁ፡፡












**ዐይን፡** እኔ ባላይላችሁ ኖሮ፤ማየት አትችሉም ነበር፡፡

**ጆሮ፡** አንተ ተዉ....ወደ እናንተ የሚመጣ ክፉ እና መልካም ድምጽ ባልለይ ኖሮ፤እንዴት ትሆኑ ነበር፡፡

**ቆዳ፡** እናንተ ለምን ትጣላላችሁ፤ እኔን የሚጋጭ ነገር ባልጠብቅ ኖሮ፤ መኖራችሁ ከባድ ነበር፡፡

**ምላስ፡** አልክ...እኔ የምግቡን ጣዕም ጥፍጥና እና መራራነቱን ባልለይ በራሃብ ትሞቱ ነበር፡፡

**አፍንጫ፡** እኔ ሽታን ባልለይላችሁ ኖሮ፡ሁላችሁም ጥሩ እና መጥፎ መዓዛ አትለዩም ነበር፡፡

## ተከታታይ ምዘና

- የቡድን ትዕይንት ወይም ማሳያ
- የግል እና ቡድን
- ፖርትፎሊዮ
- የቃል ጥያቄ
- በመጨረሻ መልመጃዎችን በማሰራት ግንዛቤዎቻቸዉን አረጋግጥ/ጪ፡፡

**የመልመጃ 1 መልስ**

ተማሪዎችግንዛቤዎቻቸዉን በደንብ እንዲገልፁ ምራቸዉ/ሪአቸዉ፡፡

# የሥነጥበባት ትምህርት ሲለበስ

# ሦስተኛ ክፍል

**የመማር ዉጤቶች፡**

**በዚህ ምዕራፍ ትምህርት መጨረሻ ተማሪዎች:**

- ✓ የሙዚቃ ኖታዎች (እስከ ሩብ ኖታና ማረፊያዎቻቸዉ)፣ መሰረታዊ ቀለሞች፣ የስነ ስዕል ዘዴዎችና ድራማ ይረዳሉ፤
- ✓ ብቀላል የሙዚቃ ኖታ የተፃፉ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ተጫዉተዉ በተግባር ያሳያሉ፤
- ✓ የቤተሰብ ተግባራትን እንደምሳሌ በመዉሰድ በዜማና በዉዝዋዜ እያስመሰሉ ሚና በመጫወት ማሳየት ይችላሉ፤
- ✓ የቀለማት ቅይጥን፣ የፅህፈትንና ቅለማን በመጠቀም ንድፍን በተግባር ማሳየት ይችላሉ፤
- ✓ የአከባቢያቸዉን ባህል ከስነጥበባት አንፃር አነፃፅረዉ የተነትናሉ፤
- ✓ የቀድሞና የወቅቱን ዝማሬ እንዲሁም ታዋቂ ባህላዊ ዉዝዋዜን ይለያሉ፤
- ✓ በአከባቢያቸዉ የሚገኙትን ታሪካዊ ቦታዎችንና ቤተመዘክሮችን በመጎብኘት ይዘግባላ፤
- ✓ የሀገራችንን የስነጥበብ ሥራዎችን በዜማ፤ በትዕይንት፣ በዉዝዋዜና ሚና በመጫወት ያደንቃሉ፡፡

| የሥነጥበባት ትምህርት ሲለበስ<br>ሦስተኛ ክፍል | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የትምህርት ዐበይት ነጥቦች | ይዘት | የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ | የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች | ምዘናና ክትትል |
| ስነጥበባትን መረዳት | **ምዕራፍ 1:**<br>1. ስነጥበባትን መለየትና መግለፅ (ክፍለ ጊዜ 25)<br>1.1 የሙዚቃ ኖታዎች (እስከ ግማሽ ኖታና ማረፊያው) (ክፍለ ጊዜ 8)<br>1.2 መሠረታዊ ቀለማት (ክፍለ ጊዜ 8)<br>1.3 ስነስዕልና የድራማ ጨዋታ (ክፍለ ጊዜ 9) | ☞ ተማሪዎችን ሩብ ሙዚቃ ኖታንና ማረፊያዉን ማንመበብ ማለማመድ<br>☞ በተግባር እያሳዩ ማስተማር<br>☞ የቪዲዮ ምስል፣ እንቅስቃሴና መልዕክት አይተዉ እንዲረዱ ማድረግ | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ ምስልና የቪዲዮ ማጫወቻ | • ምልከታ<br>• የግልና የቡድን ገለፃ<br>• ፈተና |
| የፈጠራ ክሂሎት | **ምዕራፍ 2:**<br>2. የስነጥበብ ልምምድ (ክፍለ ጊዜ 27)<br>2.1 የሙዚቃ ድምፆች፣ ኖታዎችና የሙዚቃ መሳሪያ ምት (ክፍለ ጊዜ 8)<br>2.2 ቀላል ቅርፆችን ማቅለም<br>(ክፍለ ጊዜ 8)<br>2.3 የመሰረታዊ ቀለማት ቅየጣና | ☞ ኖታዎችን መፃፍና ማንበብ ማለማመድ<br>☞ በተግባር እያሳዩ ማስተማር<br>☞ የቤተሰብ አባላትሚናዎችን እንደ አብነት በመዉሰድ በዜማ፣ በዉዝዋዜ፣ በማስመሰልና ሚና በመጫወት ማሳየት<br>☞ የንድፍ ስራ፣ የቀለማት ቅየጣ፣ ህትመትና ማቀለምን ማለማመድ | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ እረሳስ፣ የዉሃ ቀለም መቀቢያ፣ የዉሃ ቀለምና በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የንድፍ ስራ መሳሪያዎች | • ምልከታ<br>• የግልና የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ<br>• ፈተና |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የህትመት አቅጣጫ (ክፍለ ጊዜ 10)<br><br>2.4 የድራማ፣ የቪዲዮና የዐዉደሪዕይ መልዕክቶች (ክፍለ ጊዜ 12) | | | |
| ባህላዊና ተጨባጭ ሁኔታዎች | **ምዕራፍ 3:**<br><br>3. የባህል ገለፃ (ክፍለ ጊዜ 20)<br>3.1 የተለያዩ ባህል ታሪካዊ ክስተቶች በስነጥበብ ዉስጥ:-<br>- የቀድሞ<br>- የአሁን | ☞ የተለያዩ ባህል ታሪካዊ ክስተቶችን በዜማ፣ በዉዝዋዜ፣ በማስመሰል፣ ሚና በመጫወትና በመሳሰሉት ማስተማር<br>☞ በምልከታ ማስተማር | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ እርሳስ፣ ክራወንና ጠስትል፣ ከሰል፣ የዉሃ ቀለም፣ የዘይት ቀለም፣ በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የስነጥበብ ስራ መሳሪያዎች | ▪ ምልከታ<br>▪ የግልና የቡድን ገለፃ<br>▪ ፖርትፎሊዮ<br>▪ የቃል ጥያቄ<br>▪ ፈተና |
| የስነጥበባት ሳቢነት | **ምዕራፍ 4:**<br><br>4. የስንጥበብ ስራዎችን ማድነቅ (ክፍለ ጊዜ 25)<br>4.1 የሀገራችን ባህላዊ ስነጥበባት (ዐዉደርዕይ፣ ሙዚቃና ትያትር) | ☞ ሰርተዉ በማሳየት ማስተማር (የሠረገ ዘፈን፣ ቀረርቶ፣ የእረኞች ዘፈንና የመሳሰሉትን እያዜሙ፡ ሚናን በመጫወት ምስሎችን አስመስለዉ እንዲስሉ ማሰራት)<br>☞ በገለፃ ማስተማር | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ እረሳስ፣ ክራወን በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የንድፍ ስራ መሳሪያዎች | • ምልከታ<br>• የግልና የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ<br>• የቃል ጥያቄ<br>• ፈተና |
| ትስስር፣ ግንኙነትና ተግባራዊነት | **ምዕራፍ 5:**<br><br>5. የትምህርት ግንኙነት (ክፍለ ጊዜ 20)<br>5.1 በስነጥበባት መካከል የሚገኝ ግንኙነት (ክፍለ | ☞ ተማሪዎች ስለ የተፈጥሮ ቀለማት ሚናን እየተጫወቱ፣ በቀላል ምት እየተወዛወዙ እንዲያዜሙ ማነቃቃት<br>☞ ተማርዎች ስለ ተፈጥሯዊ | ▪ የልምምድ ክፍል<br>▪ የቪዲዮ ማጫወቻና ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች<br>▪ እርሳስ፣ ክራወንና ጠስትል፣ ከሰል፣ የዉሃ | • ምልከታ<br>• የግልና የቡድን ገለፃ<br>• ፖርትፎሊዮ<br>• የቃል ጥያቄ<br>• ፈተና |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ጊዜ 9)<br>5.2 የስነጥበባት ክሂሎት ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ለመማር የሚኖራቸዉን ጥቅሞች (ክፍለ ጊዜ 11) | ቀለማትሚና እየተጫወቱ በቀላል ምት እተወዛወዙ እንዲያዜሙ ማነቃቃት<br>.<br>☞ የስነጥበባት ክሂሎትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማዋሀድ ማስተማር (ንፅህና፣ የስሜት ህዋሳት፣ የተክሎች እንክብካቤና የመሳሰሉትን እንዲያዜሙ ማነሳሳት) | ቀለም፣ የዘይት ቀለም፣ በአከባቢያቸዉ የሚገኙ የስነጥበብ ስራ መሳሪያዎች | |